# ሞጁል  አምስት

# የኤክሳይዝ ታክስ ሥልጠና ሞጁል 5 ሞጁል

## ምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

### መግቢያ

ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ እንደ ቀጥታ ታክስ ከግለሰብ ወይም ከድርጅት ከሚገኘው ገቢ በቀጥታ ግለሰቡ ወይም ድርጅቱ ራሱ የሚከፍለው ሳይሆን በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ በተመረቱ ምርቶችና አገልግሎቶች ከተጠቃሚው የሚሰበሰብ ታክስ ነው፡፡ ቀጥተኛ ያልሆኑ የታክስ ዓይነቶች ውስጥ ኤክሳይዝ ታክስ አንዱ ሲሆን የተጨማሪ

እሴት ታክስ /VAT/እና የቴምብር ቀረጥ ይገኙበታል። ኤክሳይዝ ታክስ የቅንጦት ዕቃዎች ላይ እንዲሁም የህብረተሰቡን ጤንነት የሚጎዱና ማህበራዊ ችግር የሚያስከትሉ ዕቃዎችን አጠቃቀም ለመቀነስ ሲባል የሚጣል ታክስ ነው።

በዘመናዊ መልክ ታክሱ መጣል የተጀመረው በሆላንድ 17ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን በሕግ የተደነገገው በእንግሊዝ በ1643 ነው። ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ በስፋት እየተስፋፋ ሄዶ አሁን በሁሉም ሀገር በሚባል ደረጃ ኤክሳይዝ ታክስ ይሰበሰባል። ይሁን እንጂ የታክሱ መጣኔው እና የሚጣልባቸው ዕቃዎች እንደየ ሀገሩ የተወሰኑ ልዩነት ቢኖራቸውም በሁሉም ሀገር ተግባራዊ ሆኗል ማለት ይቻላል።

ኤክሳይዝ ታክስ፤ በሀገራችን ኢትዮጵያ የተጀመረው በ1935 ሲሆን "በዘመናዊ መልክ ወጡ" ከሚባሉ ሕጎች ከመጀመሪያዎቹ መካከል ይገኛል። አዋጅ ቁጥር 40/1935፤ ከ1935 ጀምሮ እስከ 1995 እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 307/95 በፊት ባሉት ሕጎች፤ ታክሱ በሚጣልባቸው ዕቃዎች፣ መጣኔ የተወሰኑ ማሻሻያዎች እየተደረገባቸው፣ በተመረተ በ3 ቀን ጊዜ ውስጥ ታክሱ ሊከፈል እንደሚገባ፣ በዕቃዎች ላይ የሚጣለው መጠን በadvalorem እና በቁርጥ ወይም ሁለቱንም ያካተተ መሆኑ፣ በተጨማሪም የቁጥጥር ሁኔታው በግልጽ የተቀመጠና ማለትም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር (በገቢዎች መ/ቤት) ቁጥጥር እየተደረገበት እንደሚከናወን ይገልፃሉ። ለዚህ ምሳሌም ቢራን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል።

የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ዓይነት እንደገና በመፈተሽ በትክክል የቅንጦት ዕቃዎች ናቸው በሚባሉ፣ የኅብረተሰቡን ጤና በሚጎዱ እና የማህበራዊ ችግር በሚያስከትሉ እንዲሁም መሠረታዊ በመሆናቸው ምክንያት የገበያ ተፈላጊነታቸው በማይቀንስ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ እንዲጣል ማድረግ አስፈላጊ ሆኗል። እንዲሁም፤ በማምረቻ ወጪ ላይ ሲሰላ የነበረው የኤክሳይዝ ታክስ በፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ እንዲተካ መደረጉ ታክስ ከፋዮች ሊከፍሉት በሚገባ ታክስ ተገማችነት ረገድ ሲያጋጥማቸው የነበረውን ችግር የሚያቃልል መሆኑ ታምኖበታል። በሥራ ላይ የነበረው የኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 ባሉበት ጉድለቶች ምክንያት የኤክሳይዝ ታክስን በትክክል በመሰብሰብ ረገድ ያጋጠመውን ችግር መቅረፍ የሚያስችል አዋጅ ማውጣት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ የኤክሳይዝ

ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ወጥቷል። የገንዘብ ሚኒስቴር በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 አንቀጽ 42/2 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት አዋጁን በተሟላ መልኩ ማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ቁጥር 67/2013 አዘጋጅቷል። በመሆኑም እነዚህን መሠረት በማድረግ ለኤክሳይዝ ታክስ ግብር ከፋዮች ይህ የሥልጠና ሞጁል ተዘጋጅቷል።

# ክፍል አንድ

# አጠቃላይ ሁኔታ

## 1.1. ዓላማ

**ዋና ዓላማ**

በዚህ ሞጁል የሚሠለጥኑ ሠልጣኞች በሥልጠናው መጨረሻ:-

- የሥልጠና ሞጁሉን በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 እና በመመሪያ ቁጥር 67/2013 መሠረት በማቅረብ እና ውይይት በማድረግ ኤክሳይዝ ታክስ የሚመለከታቸው አስመጭዎች እና አምራቾች በሚያስመጧቸው እና በሚያመርቷቸው ዕቃዎች ላይ በሕግ በተቀመጠው አሠራር መሠረት ታክሱን የማሳወቅ እና የመክፈል ግዴታቸውን እንዲወጡ ያስችላል።

**ዝርዝር ዓላማ**

- የኤክሳይዝ ታክስ ምንነት እና አስፈላጊነት ይገልጻሉ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ የዋጋ መሠረት አውቀው ማስላት ይችላሉ፤
- በጥሬ ዕቃ/ግብዓት ላይ የተከፈለ ታክስ የትኛው እንደሚቀነስና እንደማይቀነስ ይለያሉ፤
- የኤክሣይዝ ታክስ ምዝገባ እና ፈቃድ እንዲሁም እገዳን ይገልጻሉ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርን ይገልጻሉ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ የሕግ አግባቡን በማስረዳት ተመላሽ የሚፈቀድባቸውን ግብይቶች ይለያሉ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ እንዴት እና መቼ እንደሚከፈል ያስረዳሉ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተጠቀሱትን አስተዳደራዊ እና ወንጀል ቅጣቶች ይለያሉ፤
- ታክሱን ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት ምን ማለት እንደሆነ ያስረዳሉ።

## 1.2. ውጤት

**ከዚህ ሥልጠና በኋላ ሠልጣኞች:-**

- ታክስ ከፋዮች ስለኤክሳይዝ ታክስ ምዝገባ፣ ስረዛ፣ ማቀናነስ፣ ስለተመላሽ፣ አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣቶች እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በቂ እውቀት ያገኛሉ።

- ሕግ እና ሥርዓቱን መሠረት በማድረግ ወቅቱን ጠብቆ የኤክሳይዝ ታክስን አሳውቀው ይከፍላሉ።

## 1.3. ወሰን

- **የሰነዱ ሽፋን**

ሰነዱ የሚሸፍነው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 እና አዋጁን በተሟላ መልኩ ለማስፈጸም የወጣው መመሪያ ቁጥር 67/2013 ነው።

- **የሥልጠና ተሳታፊዎች**

ሥልጠናው መሠረታዊ እንደመሆኑ ለኤክሳይዝ ታክስ ግብር ከፋዮች እና በግብር ከፋዩ ድርጅት ለሚሠሩ በድርጅቱ ሠራተኞነታቸው የተረጋገጠላቸው ባለሙያዎች ይሰጣል።

- **ጊዜ**

ሥልጠናው የሚሰጠው ለዘጠኝ ሰዓታት ነው።

## 1.4. ትርጓሜ

- “ፋብሪካ” ማለት ፈቃድ የተሰጠው አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የሚያመርትበት ወይም የሚያከማችበት ሥፍራ ሲሆን፣ ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ ለገበያ የሚቀርቡበትን ማናቸውንም የአምራቹን የሥራ ቦታ አይጨምርም።
- “ማምረት” ማለት:-

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ማምረት፤

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች በማምረት ሂደት ማናቸውንም ግብአት ወይም በከፊል የተጠናቀቀ ምርት ማምረት ወይም

ሐ) አልኮልን ማጣራት፣ ማሻሻል፣ ለሚፈለገው አገልግሎት ማዘጋጀት፣ ለሰው አገልግሎት እንዳይውል ማድረግን ይጨምራል።

- **“የታክስ ባለሥልጣን”:-** ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር እንዲሁም የየክልሉ እና የከተማ አስተዳደሮች የገቢ ሰብሳቢ አካላት ናቸው።

# ክፍል ሁለት

## የኤክሳይዝ ታክስ ምንነትና አስፈላጊነት እንዲሁም አከፋፈል

### 2.1. የኤክሳይዝ ታክስ ምንነት

- በኦኢሲዲ ትርጉም:- በድርጊት፣ በሙያ፣ በልዩ ጥቅም፣ በማምረት፣ በመሸጥ ወይም በመጠቀም ላይ የሚጣል ታክስ ነው።
- የተለመደ ዓለም አቀፍ ትርጉም:- የተወሰኑ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በሚመረቱበት፣ በሚሸጡበት ወይም ጥቅም ላይ በሚውሉበት ጊዜ የሚከፈል ታክስ ነው።
- በኢትዮጵያ:- "የኤክሳይዝ ታክስ" ተብሎ የሚታወቅ ታክስ በሚከተሉት ላይ ተጥሏል:-

  ሀ) በተፈቀደለት አምራች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች እና

  ለ) ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች። በኢትዮጵያ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ የተፈቀደለት አምራች እና ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ አስመጪው የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

- ታክሱ የሚጣለው በተወሰኑ የቅንጦት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር በሚያስከትሉ እና በዋጋቸው መጨመር ምክንያት ፍጆታቸው በማይቀንስ ዕቃዎች ላይ ነው፤
  - የቅንጦት ዕቃዎች አስፈላጊ በመሆናቸው ሳይሆን የኢኮኖሚ ደረጃን ለማሳየት ወይም አትኩሮትን ለመሳብ ጥቅም ላይ የሚውሉ ዕቃዎች ናቸው።
  - ጉዳት የሚያስከትሉ ዕቃዎች በተጠቃሚው ጤና ማህበራዊ ኑሮ እና ኢኮኖሚ ላይ ችግር የሚያስከትሉ ዕቃዎች/የኃጢአት ታክስ ናቸው።
  - ፍጆታቸው የማይቀንስ ዕቃዎች ዋጋቸው በመጨመሩ ምክንያት እምብዛም የፍላጐት/የፍጆታ መቀነስ የማይታይባቸው ዕቃዎች ናቸው።

### 2.2. የኤክሳይዝ ታክስ አስፈላጊነት

- **ገቢ ለመሰብሰብ:-** የኤክሣይዝ ታክስ በተጣለባቸው ዕቃዎች ፍጆታ ምክንያት የሚደርሰውን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ የጤና ችግር ለመቋቋም (በሲጋራ/ የሳንባ፣ በመጠጥ/የትራፊክ አደጋ ወ.ዘ.ተ) መንግሥት የሚያወጣውን ወጪ ለመሸፈን፤
- **የኅብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ:-** ሰዎች በዋጋው መብዛት ምክንያት እንደ ሲጋራ እና አልኮል የመሳሰሉ ምርቶችን መጠቀማቸውን እንዲቀንሱ፤
- **ሀብትን ለማደላደል:-** ሀብታሞች ከሚጠቀሙባቸው የቅንጦት ዕቃዎች ታክስ በመሰብሰብ ድሃው ኅብረተሰብ የሚጠቀምባቸውን የልማት ሥራዎች ለመሥራት፤
- **አካባቢ ጥበቃ:-** በአካባቢ ደኅንነት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ እንደ ነዳጅ፣ የፕላስቲክ ዕቃዎች ያሉ ዕቃዎችን አጠቃቀም መቀነስ።

**መከራ 1**

1. የኤክሳይዝ ታክስ አስፈላጊነት ሁለቱን ጥቀስ/ሽ?

## 2.3. የታክሱ መጣኔ

- የኤክሳይዝ ታክስ ከ 5% ጀምሮ እስከ 100% የተጣለ ሲሆን በመኪናዎች ላይ ብቻ ግን የአገልግሎት ዘመናቸውን፣ የሲ.ሲ. መጠናቸውን መሠረት አድርጎ ከ 100% በላይ እስከ 500% ተጥሎባቸዋል። ይህ ማለት የሲ.ሲ. መጠን 1300 በላይ ያላቸው እና የአገልግሎት ዘመናቸው ረጅም የሆነ የታክስ መጣኔያቸው በአንፃራያዊነት ከፍተኛ ነው።

## 2.4. በተፈቀደለት አምራች የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ

የተፈቀደለት አምራች የመጨረሻውን ምርት ለማምረት የሚጠቀምባቸውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ጥሬ ዕቃዎች ራሱ የሚያመርት እና የኤክሳይዝ ታክሱ ስሌት በዋጋው በመቶኛ በሚሆንበት ጊዜ የጥሬ ዕቃው ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው ትክክለኛው የገበያ ዋጋ ነው። "ትክክለኛ ዋጋ ነው" የሚባለው ጥሬ ዕቃውን ለማምረት የሚወጣው ወጪ እና ጥሬ ዕቃው ለሦስተኛ ወገን ቢሸጥ የሚታከለውን የትርፍ ህዳግ የሚያጠቃልል ይሆናል።

የተፈቀደለት አምራች ጥሬ ዕቃውን ለሦስተኛ ወገን ጭምር የሚሸጥ ከሆነ፣ ለሦስተኛ ወገን የተሸጠበት ዋጋ የመጨረሻውን ምርት ለሚያመርተው ፋብሪካም ጥሬ ዕቃው የተሸጠበት ዋጋ እንደሆነ ይቆጠራል። በዚህ መሠረት የሚወሰነው የእያንዳንዱ ጥሬ ዕቃ ዋጋ የተፈቀደለት አምራች በሚያቀርበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ መካተት አለበት።

## 2.5. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ጊዜ

የተፈቀደለት አምራች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያመርታቸው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የተመረቱት ዕቃዎች ከአምራቹ ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ የኤክሳይዝ ታክሱን የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል። ለዚህ በተፈቀደለት አምራች ፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ዕቃዎች ጥቅም ላይ በዋሉበት ጊዜ ከፋብሪካው እንደወጡ ይቆጠራል። የተፈቀደለት አምራች በአንድ ወር ውስጥ ከማምረቻው ፋብሪካ ወጪ ባደረጋቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚቀጥለው ወር 30ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት።

ከዋጋ ዝርዝር፣ ከማስረከቢያ ሰነድ እና ከደረሰኝ ጋር ማመሳከር እንዲቻል በኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ቅጽ ውስጥ የእያንዳንዱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ዓይነት እና ለሽያጭ ከተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ወጥቶ ሳይሸጥ የተመለሰው ተለይቶ ማስታወቂያ ሊቀርብበት ይገባል። የታክሱ ባለሥልጣን በእያንዳንዱ የታክስ ማስታወቂያ ላይ የተመለከተውን መረጃ በተፈቀደለት አምራች ከሚያዘው የምርት፣ በመጋዘን የሚገኝ ዕቃ እና የሽያጭ መረጃ ጋር ማመሳከር አለበት። የተፈቀደለት አምራች የታክስ ማስታወቂያውን ትክክለኛነት የሚያስረዱ ደረሰኞችን፣ የዕቃ ማስረከቢያ ሰነዶችን እና የየዕለቱን የኤክሳይዝ ታክስ መረጃ በሚገባ መያዝ አለበት።

አስመጪ ወደ ሀገር ውስጥ ባስገባቸው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎቹ ወደ ሀገር በገቡበት ጊዜ ለታክሱ ባለሥልጣን መክፈል አለበት። ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ታክሱ የሚሠላው፣ የሚከፈለው፣ ሂሳቡ የሚያዘው እና የታክሱ ዕዳ በአስገዳጅነት የሚሰበሰበው በጉምሩክ ሕግ መሠረት ይሆናል።

## 2.6. ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች

የሚከተሉት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ተደርገዋል:-

- ከዚህ ሞጁል ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 2 የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ዕቃዎች፤
- የተፈቀደለት የዕቃ መጋዘንን ጨምሮ በባለሥልጣኑ ቁጥጥር ሥር ሆነው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ዕቃዎች፤

- ከታክሱ ባለሥልጣን አስቀድሞ በተሰጠ የፅሑፍ ፈቃድ መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኞች በተገኙበት ከተመረቱበት ፋብሪካ ከመውጣታቸው በፊት በአምራቹ ከጥቅም ውጪ እንዲሆኑ የተደረጉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፤
- ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የመሆን መብት ላላቸው አካላት የሚሸጡ ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፤
- ለኢኮኖሚ፣ ለማህበራዊና ለአስተዳደራዊ ምክንያቶች በሚኒስትሩ (የገንዘብ ሚኒስቴር) ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች፤
- ለሕክምና አገልግሎት እንዲውል ለሰው በመጠጥነት አገልግሎት ሊሰጥ በማይችልበት አኳኋን የተመረተ አልኮል፤
- በሚከተለው ሁኔታ በአደጋ ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የጠፉ ወይም የተበላሹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች:-

(ሀ) ዕቃዎች የመጫን ወይም የማውረድ ተግባርን ጨምሮ ዕቃዎቹ ከአምራቹ ፋብሪካ በመውጣት ላይ ባሉበት ጊዜ፣

(ለ) ከፋብሪካው ከመውጣታቸው በፊት ዕቃዎቹ በተመረቱበት በአምራቹ ፋብሪካ ውስጥ ባሉበት ጊዜ እንዲሁም

(ሐ) ዕቃዎቹ ኢትዮጵያ ከመድረሳቸው በፊት በአውሮፕላን ወይም በመርከብ በመጓጓዝ ላይ ባሉበት ጊዜ። የተፈቀደለት አምራች በአደጋ ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለጠፉ ወይም ለተበላሹ ዕቃዎች ካሣ ያገኘ እንደሆነ እና ካሣው የኤክሳይዝ ታክሱን የሚጨምር ከሆነ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የመሆን መብት ላላቸው አካላት የሚሸጡ ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም።

## 2.7. የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ የስሌት መሠረት

ቀደም ሲል የማምረቻ ወጪን መሠረት በማድረግ ሲሰላ የነበረው ኤክሳይዝ ታክስ በአዲሱ ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ በፋብሪካ መሸጫ ዋጋ እንዲተካ ተደርጓል። ይህም ታክስ ከፋዮች ሊከፍሉት በሚገባ ታክስ የተገማችነት ችግር ለማቃለል ታስቦ የተደረገ ማሻሻያ ነው። በዚህ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ዋጋ:-

- ወደ ኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ዋጋ በዕቃው ላይ የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈል ቢሆንም ባይሆንም በጉምሩክ አዋጅ መሠረት የሚሰላው የዕቃው ዋጋ እና በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባው የጉምሩክ ቀረጥ ድምር ነው።

- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ሲሆን የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የኤክሣይዝ ቴምብር (ካለ) ወጪ እና የተመላሽ ዕቃ መያዣ ወጪ አይጨምርም።

ምሳሌ:- አንድ የመኪና አስመጭ፤ የውጭ ምንዛሬው በኢትዮጵያ ብር 400,000 (አራት መቶ ሺህ ብር) የሆነ የሲሊንደር ይዘቱ ከ 1,000 ሲሲ ያልበለጠ አዲስ ሞዴል መኪና ከውጭ ሀገር ገዛ። ይህ አስመጭ ለትራንስፖርትና ሌሎች ወጪዎች ብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) አወጣ እና የመኪናው አጠቃላይ ወጪ ብር 450,000 (አራት መቶ ሃምሳ ሺህ) ሆነ። በዚህ መሠረት ኤክሳይዝ ታክሱ እንደሚከተለው ይሰላል፤

- ኤክሳይዝ ታክስ ከጉምሩክ ቀረጥ በኋላ የሚሰላ በመሆኑ መጀመሪያ የጉምሩክ ቀረጥ ይሰላል:-

የጉምሩክ ቀረጥ = 35%

የመኪና ጠቅላላ ዋጋ = 450,000

የመኪና ጠቅላላ ዋጋ × የጉምሩክ ቀረጥ (450,000 × 35%) = 157,500

የጉምሩክ ቀረጥ = 157,500

- በሁለተኛ ደረጃ ኤክሳይዝ ታክስ ይሰላል፤

ኤክሳይዝ ታክስ = 5% (መኪናው አዲስ እና ከ 1,000 ሲሲ ያልበለጠ ስለሆነ) ጠቅላላ ዋጋ + የጉምሩክ ቀረጥ (607,500) × ኤክሳይዝ ታክስ (5%) = 30,375 ኤክሳይዝ ታክስ = 30,375

ስለዚህ ኤክሳይዝ ታክሱን ጨምሮ የመኪናው ዋጋ 637,875 የደረሰ ሲሆን ከዚህ በኋላ የተጨማሪ እሴት ታክስ (15%) እንዲሁም ዊዝሆልዲግ ታክስ (3%)፣ .. ይሰላል።

**ሙከራ 2**

1. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው እና ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች መጣኔ በመለየት ታክሱን በምሳሌ አስሉ?

## 2.8. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ ሆኖ የሚቆጠረው:-

- ✓ ለታክሱ ባለሥልጣን በእያንዳንዱ ወር ከ30ኛው ቀን በፊት በሚቀጥለው ወር ከፋብሪካው የሚወጡ ዕቃዎች የሚቀርበው ዋጋ ዝርዝር ይሆናል።
- ✓ ታክስ ከፋዩ የሚያቀርበው የዋጋ ዝርዝር ለእያንዳንዱ ምርት ዓይነት፣ መያዣ እና የመያዣ ዓይነት የሚኖረውን ዋጋ የሚያመለክት መሆን አለበት።
- ✓ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆነው ምርቱን ወደ ገዥው ለማድረስ የሚወጣውን የትራንስፖርት ሂሳብ የሚጨምር አይሆንም።

- ✓ የታክሱ ባለሥልጣን ምርቱ የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልበት ወደ ገበያ መቅረቡን ወይም ታክስ ከፋዩ የገለፀው ዋጋ የገበያ ዋጋ በታች መሆኑን ያረጋገጠ እንደሆነ ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ዋጋውን ይወስናል፡፡
- ✓ የታክሱ ባለሥልጣን ትክክለኛ ዋጋን መሠረት በማድረግ የሚከፈለውን ታክስ የሚወስነው ታክስ ከፋዩ ያስታወቀው ዋጋ ከገበያ ዋጋ በታች ከሆነ፣ ምርቱ ታክስ ሳይከፈልበት ለገበያ ከቀረበ፣ ወይም ምርቱ ፈቃድ በሌለው ሰው የተመረተ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡
- ✓ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ሆኖ የሚቆጠረውና ለኤክሳይዝ ታክስ ክፍያ መሠረት የሚሆነው ሌላ የተፈቀደለት አምራች ለተመሳሳይ ዕቃዎች የሚያስከፍለው ዋጋ ሊሆን ይችላል፡፡
- ✓ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ከመያዣው ጋር አብሮ የሚሸጥ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው በጠቅላላው ዋጋ ላይ ይሆናል፡፡ ሆኖም መያዣው ተመላሽ የሚደረግ ከሆነ በመያዣው ዋጋ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልም፡፡
- ✓ የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን የመጨረሻ ምርቶች ለማምረት የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎች የሚጠቀም በሚሆንበት ጊዜ የሚያዘጋጀው የዕቃዎች ዋጋ ዝርዝር የእነዚህን ጥሬ ዕቃዎች ዋጋ የሚጨምር መሆን አለበት፡፡ ስለሆነም የንፁህ አልኮል በሊትር የሚኖረው ዋጋ እና የትምባሆ ቅጠል በኪሎ ግራም የሚኖረው ዋጋ በዝርዝሩ ውስጥ መካተት ይኖርበታል፡፡

## 2.9. ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር አቀራረብ

- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት የሚከናወንበት ዋጋ ግልፅ እንዲሆን እና አምራቾች በእኩል መወዳደር እንዲችሉ እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች የምርቱን ዋጋ ዝርዝር በምርት ዓይነት፣ በመያዣው መጠን እና ዓይነት እንዲሁም ለገበያ በሚውልበት ቦታ በመለየት ለታክሱ ባለሥልጣን በየወሩ ማቅረብ አለበት፡፡
- ወርሀዊ የዋጋ ዝርዝር የሚዘጋጅበትና የሚቀርብበት ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለሚያመርቱ አምራቾች በተዘጋጀው ማንዋል ውስጥ በዝርዝር ይመለከታል፡፡
- የእያንዳንዱን የምርት ዓይነት፣ የነጠላውን መጠን እና ዓይነት የሚያሳየው የዋጋ ዝርዝር የእያንዳንዱን ምርት የማምረቻ ወጪ እና የትርፍ ህዳግ የያዘ ሊሆን ይገባል፡፡

- ዕቃው ለታክሱ ባለሥልጣን በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ከተመለከተው ዋጋ በላይ የተሸጠ እንደሆነ ለኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆነው በደረሰኙ ላይ የተመለከተው ዕቃው የተሸጠበት ትክክለኛ ዋጋ ይሆናል።
- ዕቃው ለታክሱ ባለሥልጣን በቀረበው የዋጋ ዝርዝር ውስጥ ከተመለከተው ዋጋ በታች የተሸጠ እንደሆነ ወይም ከተፈቀደለት ፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ ዋጋው ያልተከፈለበት ከሆነ ከፋብሪካው በወጣው ዕቃ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰላው በቀረበው የዋጋ ዝርዝር በተመለከተው ዋጋ መሠረት ይሆናል።
- ዕቃው ከፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ የሚዘጋጀው የዕቃ ማስረከቢያ ሰነድ እና/ወይም ደረሰኝ የሚከተሉትን መረጃዎች ሊይዝ ይገባል:-

ሀ) ዕቃው ከፋብሪካው የወጣበት ቀን፣ ለ) የዕቃውን ማስረከቢያ ቦታ፣

ሐ) የደንበኛውን ስም ወይም ሽያጭ ከመከናወኑ በፊት ከፋብሪካ የሚወጣ ከሆነ ይህንኑ፣

መ) ደንበኛው ከተፈቀደለት አምራች ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ከሆነ ይህንኑ፣ ሠ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ዓይነት፣

ረ) የዕቃዎቹን ብዛት፣

ሰ) የእያንዳንዱን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ዋጋ፣ ሸ) ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ።

## 2.10. የዕቃ ቆጠራ እና የጠፉ ዕቃዎች

እያንዳንዱ የተፈቀደለት አምራች በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ ጥሬ ዕቃዎችን ጨምሮ በፋብሪካው ውስጥ በሚገኝ ዕቃዎች ላይ በየዓመቱ የተሟላ ቆጠራ ማካሄድ አለበት። ከዚህም በተጨማሪ የተፈቀደለት አምራች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያሳይ ተከታታይነት ያለው ወርሀዊ ቆጠራ ማካሄድ አለበት:-

- በእያንዳንዱ ወር መጨረሻ በፋብሪካው ውስጥ የሚገኘውን ጥሬ ዕቃና የመጨረሻ ምርት፣
- አዲስ ወደ ፋብሪካው የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን፣
- በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎችን፣
- በፋብሪካው የተመረቱ የመጨረሻ ምርቶችን፣
- በፋብሪካው ተመርተው ወደ ፋብሪካው መጋዘን የገቡ ዕቃዎችን፣
- የኤክሳይዝ ታክስ ተከፍሎባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ ዕቃዎችን፣

- የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፍልባቸው ከፋብሪካው ቅጥር ግቢ የወጡ ዕቃዎችን፣
- የታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰነው መሠረት በአደጋ ምክንያት ከጥቅም ውጪ የሆኑ ዕቃዎችን።

የተፈቀደለት አምራች ለውጭ ገበያ የተላኩ ዕቃዎችን የሚመለከት የተሟላ መረጃ መያዝ አለበት። ዕቃዎች የጠፉ መሆኑን የሚያረጋግጥ የዕቃው መጥፋት በታወቀበት ጊዜ ወዲያውኑ ሪፖርት የተደረገና አግባብ ባለው የፀጥታ አካል ምርመራ ተካሂዶ የዕቃው መጥፋት የተረጋገጠ ሲሆን ብቻ ነው። ከዚህ በላይ በተገለፀው አኳኋን መጥፋቱ ባልተረጋገጠ ዕቃ ላይ ተገቢው የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈላል። በእያንዳንዱ የተፈቀደለት ፋብሪካ ቆጠራ ከመካሄዱ ከ 14 ቀን በፊት የታክሱ ባለሥልጣን ይህንኑ እንዲያውቀው መደረግ አለበት። ቆጠራ በሚካሄድበት ጊዜ በፋብሪካው ውስጥ የሚካሄድ ማናቸውም የሥራ እንቅስቃሴ መቆም አለበት።

### 2.11. የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ

በፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ላይ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ በግብይቱ ደረሰኝ ላይ ተለይቶ መታየት ያለበት ሲሆን የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች "የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ነው" የሚባለው፤

- አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የሸጠው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ግብይት ለገዥው የሆነ እንደሆነ፣ ገዥው የከፈለው ዋጋ፣
- በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ዕቃው ከአምራቹ ፋብሪካ በወጣበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው።

### 2.12. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች መጠን

ይህ (የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች መጠን) ተፈፃሚ የሚሆነው ከዚህ ሞጁል ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 1 መሠረት በዕቃዎቹ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለው የዕቃዎቹን ብዛት ወይም ክብደት መሠረት ባደረገ መጠን በሚሆንበት ጊዜ ነው። በሚከተሉት ሁኔታዎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን የሚወሰነው ከዕቃው ጋር የሚሸጠውን የዕቃውን ማሸጊያ እና በውስጡ የያዘውን ክብደት መሠረት በማድረግ ይሆናል፤

- የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደ ኢትዮጵያ በሚገቡበት ወይም በተፈቀደለት አምራች ከተመረቱበት ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ ከዕቃው ጋር አብሮ ከሚሸጥ ማሸጊያ ጋር ወይም የዚህ ዓይነት ዕቃዎች በችርቻሮ በሚሸጡበት አብዛኛውን ጊዜ አብረው ከሚሸጡ ማሸጊያዎች ጋር ሲሆን፤ እና

- ማሸጊያው:-
  1. የተጣራ ክብደቱ ያልተፃፈበት ከሆነ ወይም
  2. በሚሸጥበት ጊዜ በውስጡ ያለው ይዘት በተለምዶ የሚታወቅ ባለመሆኑ ወይም አብዛኛውን ጊዜ ይዘቱ የሚታወቅ ባለመሆኑ ትክክለኛ ብዛቱን ወይም ክብደቱን ማወቅ የማይቻል ከሆነ፤
- የዕቃው ባለቤት የማሸጊያውን የተጣራ ክብደት ትክክለኛነት የታክስ ባለሥልጣኑን በሚያረካ አኳኋን ማስረዳት ካልቻለ፣ የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በማሸጊያው እና በውስጡ በያዘው ዕቃ ጠቅላላ ክብደት ላይ ይሆናል፡፡

## 2.13. በጥሬ ዕቃ/ግብዓት ላይ የተከፈለን ታክስ ስለማቀናነስ

የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ወደ ሀገር በገቡ ወይም በሀገር ውስጥ በተመረቱ ጥሬ ዕቃዎች/ግብዓቶች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የከፈለ እንደሆነ እና እነዚህን ጥሬ ዕቃዎች/ግብዓቶች የመጨረሻውን ምርት (ከዚህ በኋላ "የመጨረሻ ምርት") ለማምረት በግብዓትነት የተጠቀመባቸው ከሆነ፣ በጥሬ ዕቃዎቹ/ግብዓቶቹ ላይ የተከፈለው ታክስ በመጨረሻ ምርቶቹ ላይ ከሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ጋር እንዲቀናነስ ይደረጋል፡፡ ይህ አልኮልን፣ ትንባሆን እና ስኳርን አይጨምርም፡፡

**ሙከራ ሶስት**

1. በጥሬ ዕቃ/ግብዓት ላይ የተከፈለ ታክስ የትኛው እንደሚቀነስና እንደማይቀነስ ለዩ?

# ክፍል ሶስት ስለፈቃድ

## 3.1.ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልጋቸው ሥራዎች

ማንኛውም ሰው ከታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ካላገኘ ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ ዘንድ ካልተመዘገበ በስተቀር በሚከተሉት ሥራዎች ላይ መሠማራት አይችልም:-

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት፣

ለ) የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው ይገባል የተባሉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ማቅረብ፣

ሐ) ሚኒስትሩ ፈቃድ የማግኘት ግዴታ በሚጥልባቸው ሌሎች ሥራ ዘርፎች መሠማራት። በዚህ የተደነገገውን በመተላለፍ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ሥራ ላይ የተሠማራ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል። በዚህ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል የሚገደድ ሰው በታክስ ባለሥልጣኑ በተጠየቀ ጊዜ ታክሱን ወዲያውኑ መክፈል አለበት:: ከኤክሳይዝ ታክሱ በተጨማሪ በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል እንዲሁም ቅጣትና ወለድ እንዲከፍል ይደረጋል።

## 3.2.ለፈቃድ ማመልከቻ ስለማቅረብ

ለሚሠማራበት የሥራ መስክ ፈቃድ እንዲሰጠው ለታክስ ባለሥልጣኑ የሚቀርብ ማመልከቻ፤

ሀ) በተፈቀደው ቅጽ መሠረት ሊቀርብ፣ ለ)

የፈቃድ ክፍያ ሊከፈልበት፣

ሐ) በባለሥልጣኑ በተወሰነው አኳኋን ሊቀርብ ይገባል።

## 3.3.የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት

ማናቸውም ሰው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ እንዲሰጠው ሲያመለክት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት:-

ሀ) ማመልከቻው በተፈቀደው ቅጽ መሠረት መቅረብ አለበት፣

ለ) ከማመልከቻው ጋር የሚከተሉት ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፣

(i) የንግድ ፈቃድና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርን ጨምሮ የታክስ ባለሥልጣኑ እንዲቀርቡ የሚጠይቃቸው ሰነዶች፤

(ii) አመልካቹ የሚጠቀምባቸውን የአመራረት ሂደቶች፣ እንደአግባብነቱ የማምረቻውን መሣሪያዎች፣ የአልኮል ማጣሪያዎች፣ የቢራ መጥመቂያ፣ የፈሳሽ ማከማቻ፣ ኮንቴይነሮች፣ መሣሪያዎች፣ መገጣጠሚያዎች፤

(iii) የአሠራር ሂደቱን የሚገልፅ የፅሑፍ ማብራሪያ፤

(iii) ፈቃድ እንዲሰጥ ጥያቄ የቀረበበትን የማምረቻ ሕንፃ ፕላን፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች እንዲሁም ሕንፃው፣ ክፍሎች ወይም ሌሎች ቦታዎች የሚገኙበትን ሁኔታ እና አካባቢውን፤

(v) የእያንዳንዱን በፋብሪካው የተገጠመ የማምረቻ መሣሪያ የማምረት አቅም በዝርዝር፤

(vi) የማምረቻ መሣሪያዎችን በማስረጃዎች እና መግለጫዎች፤

(vii) ፈቃድ ለማግኘት እንዲሟሉ የሚጠበቁ መሣሪያዎችን፣ የአመራረት ሥርዓት ወይም ሌላ ተፈላጊ ሁኔታ፤

ሐ) በዚህ መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ በተፈቀደው ቅጽ መሠረት መሆን አለበት። ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ካልተመዘገበ በስተቀር የሚከተሉትን ሥራዎች ማከናወን አይችልም:-

ሀ) የሲጋራ ማምረቻ ወረቀት እና የሲጋራ ማሸጊያ ዕቃዎችን ወደሀገር ማስገባት፤ ለ) ጥሬ ወይም በምርት ሂደት ያላለፈ ትምባሆን ወደሀገር ማስገባት፤

ሐ) ኤታኖል ወደሀገር ማስገባት፤

መ) በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ (ለ) የተዘረዘሩ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ግብዓቶች ወደሀገር ማስገባት፣

በ(ሀ) እና (ለ) ለተመለከቱት ዕቃዎች በአስመጪነት ሊመዘገብ የሚችለው የትምባሆ ምርቶችን ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ብቻ ነው።

በኤታኖል አስመጪነት ሊመዘገቡ የሚችሉት የአልኮል መጠጦችን ለማምረት ፈቃድ የተሰጣቸው እና የኤክሳይዝ ታክስ የማይከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የሚውሉ የማጣሪያ መሣሪያዎችን ወደ ሀገር ለማስገባት የሚችሉት የተመዘገቡ ሰዎች ብቻ ናቸው። በዚህ መሠረት ለመመዝገብ ማመልከቻ የሚቀርበው፣ በተፈቀደው ቅጽ መሠረት እና የታክሱ ባለሥልጣን ከሚጠይቃቸው ሰነዶች ጋር በአንድነት መሆን አለበት።

## 3.4. የማምረቻ ቦታዎችን ስለመገምገም

ማመልከቻ ሲቀርብ የታክሱ ባለሥልጣን የማምረቻ ቦታውን እና የአመራረቱን ሂደት ማመልከቻው ተሟልቶ በቀረበ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በቦታው በመገኘት መገምገም አለበት።

## 3.5.ፈቃድ ስለመስጠት

አመልካቹ ያቀረበው ማመልከቻ ከተመረመረ እና የማምረቻ ቦታው በታክሱ ባለሥልጣን ባለሙያዎች ከተገመገመ በኋላ መስፈርቶቹ መሟላታቸው ሲረጋገጥ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ የተፈቀደለት አምራች በአመራረቱ ሂደት ወይም ሌላ ማናቸውም ፈቃዱ በተሰጠበት ሁኔታ ላይ ለውጥ ማድረግ በሚፈልግበት ጊዜ አስቀድሞ ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ እንዲችል በፈቃዱ ላይ የሚመለከተው የታክሱ ባለሥልጣን አድራሻ መመልከት አለበት፡፡

የታክስ ባለሥልጣኑ የሚቀርብለትን ማመልከቻ በመመርመር ለአመልካቹ ፈቃዱን ሊሰጥ ወይም ሊከለክል ይችላል፡፡ የታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ሊከለክል የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ይሆናል፡፡

ሀ) አመልካቹ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት በታክስ መሰወር ወይም በታክስ ማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ፤

ለ) አመልካቹ በማናቸውም ሕግ እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ፤

ሐ) አመልካቹ:-

I. የከሰረ ወይም ዕዳውን ለመክፈል ያልቻለ ከሆነ፤

II. በኪሣራ ምክንያት ሀብቱ በመጣራት ላይ ያለ ወይም ባለአደራ የተሰየመበት ከሆነ፡፡

መ) ማመልከቻው የቀረበው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት ከሆነ በማመልከቻው የተመለከተው ፋብሪካ፣ ማምረቻ፣ መጋሪያ ምርቱን ለማምረት ወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለመከታተል በቂ ካልሆነ፤

ሠ) አመልካቹ በማናቸውም የታክስ ሕግ በተደነገገው መሠረት ትክክለኛውን የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ፣ ወይም በማናቸውም የታክስ ሕግ የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ በተጠየቀው መሠረት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታውን ለመወጣት ግዴታ ለመግባት ያልተስማማ፤

ረ) በፊደል ተራ (ሀ) (ለ) (ሐ) እና (ሠ) የተመለከተው ከአመልካቹ ጋር ግንኙነት ያለውን ሰው የሚመለከት ሲሆን፣ ይህ ተፈፃሚ የሚሆነው የታክስ ባለሥልጣኑ ከአመልካቹ ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ፈቃድ በተጠየቀበት የሥራ መስክ ውስጥ የሚሠማራ ለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ያለው በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

ከሚሰጠው ፈቃድ ጋር በተያያዘ የታክሱ ባለሥልጣን አስፈላጊ መስሎ ከታየው የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ወይም ገደቦች እንዲኖሩ ሊያደርግ ይችላል። የፈቃድ ማመልከቻ ለሚያቀርብ ሰው የታክስ ባለሥልጣኑ በማመልከቻው መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ 30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽሑፍ መግለጽ አለበት። ማመልከቻው ውድቅ የተደረገ ከሆነ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት መገለጽ አለበት። የሚሰጠው ፈቃድ በታክስ ባለሥልጣኑ በተሰጠው ፈቃድ ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ የሚፀና ሲሆን ካልተሠረዘ በስተቀር ላልተወሰነ ጊዜ የፀና ይሆናል።

## 3.6. የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ስለማግኘት

ማናቸውም ሰው ከገቢዎች ሚኒስቴር የተሰጠ የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ሳይኖረው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 የተዘረዘሩ ሥራዎችን ሊያከናውን አይችልም። የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት በተፈቀደለት አምራች እና በታክሱ ባለሥልጣን መካከል እንደተፈፀመ ውል ይቆጠራል። በፈቃዱ የተመለከቱ የውል ቃሎችንና ሁኔታዎችን የሚጥስ የተፈቀደለት አምራች በዚህ ሞጁል ክፍል ሰባት መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል።

የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የሚከተሉትን መረጃዎች የሚይዝ ሊሆን ይገባል:-

- የተፈቀደለትን አምራች ስም፤
- የተፈቀደለትን አምራች የግንኙነት አድራሻ (ኢሜይል፣ ፋክስ፣ ስልክ)፤
- ፈቃዱ ተፈፃሚነት መሆን የሚጀምርበትን ቀን፤
- የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያመርትበትን ፋብሪካ እና የዋናው መሥሪያ ቤት አድራሻ፤
- የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ እንዲጠቀምባቸው በታክሱ ባለሥልጣን የተፈቀደለትን መሣሪያዎች ዝርዝር፤
- የሚያመርተው ምርት ዓይነት።

የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ የተፈቀደለትን አምራች የሥራ አፈፃፀም መሠረት በማድረግ የንግድ ሥራውን የሚያካሂድባቸውን ሁኔታዎች የሚይዝ ሊሆን ይችላል። የተፈቀደለት አምራች በፈቃዱ በተዘረዘሩ መሣሪያዎች ለመጠቀም የሚችለው በፋብሪካው በተመለከተው አድራሻ ብቻ ነው። የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ምርቶች የሚመረቱበትን አድራሻ ወይም መሣሪያ ከመለወጡ በፊት፣ ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን በማስታወቅ በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ መጠየቅ አለበት። የኤክሳይዝ ታክስ

የሚከፈልባቸው ምርቶች የሚመረቱበትን አድራሻ ወይም የመሣሪያዎች መለወጥ ለታክሱ ባለሥልጣን ሳያስታውቅ እና በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ ሳይደረግ አድራሻቸውን ወይም መሣሪያዎችን የለወጠ ባለፈቃድ በዚህ ሞጁል ክፍል ሰባት መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል። የተፈቀደለት አምራች ፋብሪካ እና የማምረቻ መሣሪያዎች በአዋጁ የተደነገገውን የሚያሟሉ መሆኑ በታክሱ ባለሥልጣን ባለሙያዎች ጉብኝት ሳይረጋገጥ የኤክሳይዝ ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም።

## 3.7.የፈቃዱ ቅርጽ

የሚሰጠው ፈቃድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የሚሰጥ ይሆናል። የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለሚያመርት ሰው የሚሰጥ ፈቃድ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-

- አምራቹ እንዲያመርት የተፈቀደለትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ምድብ ወይም ምድቦች፣
- አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች እንዲያመርት የተፈቀደለትን ፋብሪካ/ፋብሪካዎች::

በዚህ መሠረት በተሰጠ ፈቃድ የተመለከተው ፋብሪካ ማምረት የሚችለው በፈቃዱ የተመለከተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ምድብ/ምድቦች ብቻ ነው። በተሰጠ ፈቃድ በተመለከተው ፋብሪካ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ማምረት የሚችለው በፈቃዱ ላይ አምራች በሚል የተመለከተው ሰው ብቻ ነው።

## 3.8.ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታዎች

ፈቃድ የተሰጠው ሰው የተሰጠውን ፈቃድ ዋንኛ ቅጂ የንግድ ሥራውን በሚያካሂድበት ዋና መሥሪያ በግልጽ በሚታይ ቦታ መለጠፍ አለበት። ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉትን መረጃዎች በሚመለከት ለታክስ ባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማስታወቂያ የመላክ ግዴታ አለበት፣

- ፈቃድ የተሰጠበትን ሥራ ያቆመ እንደሆነ፤
- የተፈቀደለት አምራች የሚያከናውነውን ዋንኛ ተግባር መጠሪያ፣ አድራሻ፣ ሥራውን የሚያከናውንበትን ቦታ፣ ባለቤትነት፣ የመተዳደሪያ ደንብ ወይም የሥራውን ባህሪ የለወጠ እንደሆነ፤
- የተፈቀደለት አምራች የሥራውን እንቅስቃሴ ለተወሰነ ጊዜ በጊዜያዊነት ያቋረጠ እንደሆነ፤ ወይም

- የተፈቀደለትን አምራች በሚመለከት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት በሚጠቀምበት በፈቃዱ በተመለከተው ፋብሪካ ወይም ማምረቻ እና መሣሪያ ላይ ለውጥ የተደረገ እንደሆነ።

የሚላከው ማስታወቂያ ለታክሱ ባለሥልጣን በሚከተለው ጊዜ ውስጥ እንዲደርስ መደረግ አለበት:-

- የሚቀርበውን ማስታወቂያ በሚመለከት የንግድ ሥራው የተዘጋው ባልታቀደ ሁኔታ ከሆነ፣ የንግድ ሥራውን ለመዝጋት ምክንያት የሆነው ሁኔታ ካጋጠመበት ቀን ጀምሮ በ7 ቀናት ውስጥ፤
- በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ማስታወቂያውን ለመላክ ምክንያት የሆነው ሁኔታ ባጋጠመ በ7 ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ እንዲደርስ መደረግ አለበት።

## 3.9. አዲስ አምራቾች

የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ያልተሰጠው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የሚፈልግ ሰው የማምረት ሥራውን ለመጀመር ካቀደበት ቀን 30 ቀን በፊት የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ እንዲሰጠው ለታክሱ ባለሥልጣን ማመልከት አለበት። የማመልከቻው ቅጽ አዲስ የሚጀመረውን የንግድ ሥራ በሚመለከት የተሟላ መረጃ ማግኘት የሚያስችል መሆን አለበት። በተለይም የንግድ ሥራው የሚመሩ ኃላፊዎች፣ የሚመረተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ምርት ዓይነት፣ የማምረቱ ተግባር የሚከናወንበትን ቦታ፣ የግብዓቱን ዓይነት፣ የግብዓት ምርት ጥመርታውን እና የማምረቻ መሣሪያውን ዓይነት የሚያካትት መሆን አለበት። የማምረቻ ቦታው በታክሱ ባለሥልጣን ከመጐብኘቱ እና አመልካቹ የማመልከቻውን ቅጽ በሚገባ ሞልቶ ከማቅረቡ በፊት ፈቃድ ሊሰጥ አይችልም።

## 3.10. ተጨማሪ ፋብሪካ ስለማቋቋም

ፈቃድ የተሰጠው ሰው በተሰጠው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ላይ ያልተመለከተ አዲስ ፋብሪካ ለማቋቋም ያቀደ እንደሆነ በፈቃዱ ላይ ማሻሻያ እንዲደረግ ወይም አዲስ ፈቃድ እንዲሰጠው መጠየቅ አለበት። ማናቸውም ሰው የታክሱ ባለሥልጣን ባለሙያዎች የማምረቻ ቦታውን ጎብኝተው የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት መጀመር አይችልም። ፈቃድ ባልተሰጠው ፋብሪካ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች የሚያመርት ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክሱን መክፈሉ

እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ሞጁል ክፍል ሰባት መሠረት አስተዳደራዊና የወንጀል ቅጣት ይቀጣል።

## 3.11. ፈቃድን ስለማገድ

የታክሱ ባለሥልጣን (የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ የሚወክለው) ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የተሰጠውን ፈቃድ ማገድ ይችላል:-

- ፈቃድ የተሰጠው ሰው ተገቢውን የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ወይም ማናቸውንም የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ፤
- ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈቃዱ የተመለከቱ ሁኔታዎችን የጣሰ እንደሆነ፤
- ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለታክስ ባለሥልጣኑ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃን የሰጠ እንደሆነ፤
- የተፈቀደለትን አምራች በሚመለከት፣ በፈቃዱ የተመለከተው ፋብሪካ፣ ማምረቻ ወይም መጋዘኛ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት ከዚያን ጊዜ በኋላ አጥጋቢ ሆነው ያልተገኙ እንደሆነ፤
- ከአምራቹ አቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው በተፈቀደለት አምራች የተመረተ የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለበት ዕቃ ይዞ የተገኘ እንደሆነ፣
- የተፈቀደለት አምራች በፈቃዱ ወይም በምዝገባው ከተመለከተው ውጪ በሆኑ ተግባራት ተሠማርቶ የተገኘ እንደሆነ፣
- ፈቃድ የተሰጠበት ተግባር በአዋጁ ወይም በሌላ ሕግ የተከለከለ እንደሆነ፣
- የተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ ወይም መጋዘኛ ከታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድ ውጪ ተለውጦ የተገኘ እንደሆነ፣

የታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድን ያገደ እንደሆነ ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ፈቃዱ የታገደ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ በጽሑፍ መስጠት አለበት። ፈቃድን ለማገድ የተሰጠ ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው። ፈቃዱ የታገደ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ የደረሰው ሰው የዕግዱ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ14 ቀናት ውስጥ ወይም የታክስ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ዕግዱን በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ የታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል በጽሑፍ ሊያቀርብ ይችላል። ፈቃድ የተሰጠው ሰው ዕግዱን በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ፣ የታክሱ ባለሥልጣን የይግባኝ ማመልከቻው በደረሰው በ14 ቀናት ውስጥ፣

- የይግባኙን አቤቱታ በመቀበል የፈቃዱን ዕገዳ ሊያነሳ፣

- ፈቃዱ የታገደበት ሰው ዕግዱ እንዲነሳለት ለማድረግ ለዕገዱ ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን በማሟላት ረገድ በማስታወቂያው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሊያከናውናቸው የሚገባ ተግባራትን የሚገልጽ ማስታወቂያ እንዲደርሰው በማድረግ፣ በማስታወቂያው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተግባራቱን ካከናወነ ዕግዱን የማንሳት፣
- ይግባኙን ውድቅ ማድረግ ፈቃዱን መሠረዝ፣ ይችላል። የታክሱ ባለሥልጣን በተጠቀሰው ጊዜ እርምጃዎችን ካልወሰደ የፈቃዱ ዕገዳ እንደተነሳ ይቆጠራል።

የኤክሳይዝ ታክስ ወይም ምዝገባ የታገደ እንደሆነ ባለፈቃዱ፣ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረቱን ተግባር ወዲያውኑ ማቆም እና የታክሱ ባለሥልጣን በሚያቀርባቸው ሁኔታዎች መሠረት መፈፀም አለበት።

የኤክሳይዝ ታክስ ፈቃድ ወይም ምዝገባ የተሠረዘ እንደሆነ:-

- ባለፈቃዱ:-

(i) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረት ወይም ወደሀገር የማስገባት ተግባሩን ማቆም፣

(ii) በእጁ በሚገኙ ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል፣

(iii) የታክሱ ባለሥልጣን በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች፣ ጥሬ ዕቃዎች፣ መሣሪያዎች፣ ቁሳቁሶች መሸጥ አለበት።

ለ) የታክሱ ባለሥልጣን፣

(i) የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወደ ሌላ ቦታ እንዲያዘዋውር፣

(ii) የመንግሥትን ገቢ ለመሰብሰብ እና የኤክሳይዝ ታክስ አዋጁን ለማስፈፀም እንዲቻል የተፈቀደለትን አምራች ፋብሪካ በቁጥጥሩ ሥር ለማድረግ ይችላል። ለዚህ አፈጻጸም ፋብሪካን በቁጥጥር ስር ማድረግ ማለት በፋብሪካው ውስጥ የተፈቀደለት አምራች የሚያከናውነው ማናቸውም ተግባር በታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድና እውቅና እንዲከናወን ማድረግ ነው።

### 3.12. ፈቃድን ስለመሠረዝ

የታክሱ ባለሥልጣን በሚከተሉት ሁኔታዎች በጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ፈቃዱን ሊሠርዝ ይችላል፣

- የታክስ ባለሥልጣኑ ማስታወቂያ የደረሰው ከሆነ፣
- በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የፈቃዱን ዕገዳ በመቃወም ይግባኝ ያላቀረበ ከሆነ፣
- በተሰጠው ማስታወቂያ ወይም በታክሱ ባለሥልጣን በተሰጠ ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በማስታወቂያው የተመለከተውን ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፣
- ፈቃዱ በመታገዱ ምክንያት የቀረበውን ይግባኝ የታክስ ባለሥልጣኑ ውድቅ ያደረገው ከሆነ።

የፈቃድ መሠረዝ ተፈፃሚ የሚሆነው ፈቃዱ መሠረዙን በሚገልጸው ማስታወቂያ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ነው። ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የተሰጠው ፈቃድ መሠረዝ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈልን እና የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብን ጨምሮ ፈቃዱ ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ባከናወነው ወይም ባላከናወነው ማናቸውም ተግባር ምክንያት በኤክሳይዝ ታክስ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ (በዚህ ሞጁል ክፍል ሰባት) መሠረት የሚኖርበትን ተጠያቂነት አያስቀርም።

## 3.13. የፈቃድ መታገድ ወይም መሠረዝ የሚኖረው ውጤት

የተፈቀደለት አምራች የተሰጠው ፈቃድ የታገደ ወይም የተሠረዘ እንደሆነ፣ **ሀ)**

**አምራቹ:-**

I. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የማምረቱን ተግባር ወዲያውኑ ማቆም፣

II. የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው በእጁ በሚገኙ እቃዎች ላይ ያልተከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ወዲያውኑ መክፈል፣

III. ከታክሱ ባለሥልጣን በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በአምራቹ ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማስወገድ አለበት።

**ለ) የታክሱ ባለሥልጣን:-**

I. የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በታክሱ ባለሥልጣን ወደፀደቀ ቦታ እንዲያዘዋውር የማዘዝ። እነዚህ ተፈፃሚ ከሚሆንባቸው ውጪ ያለ አስመጪ ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሰረዘ እንደሆነ ፈቃድ የተሰጠበትን የሥራ እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ማቆም አለበት።

II. የታክሱ ባለሥልጣን የአምራቹን ፋብሪካ እና በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች መያዝ ይችላል።

III. የታክስ ባለሥልጣኑ በፈቃዱ መታገድ ወይም መሠረዝ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካ ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የጽሑፍ ማስታወቂያ ሊሰጠው ይችላል። የዚህ ዓይነቱ ወጪ ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም እንደታክስ ይቆጠራል።

## 3.14. ፈቃድ ከመታገዱ ወይም ከመሠረዙ በፊት የታክስ ባለሥልጣኑ ሊሰጥ ስለሚገባው ማስጠንቀቂያ

የታክስ ባለሥልጣኑ የተሰጠውን ፈቃድ ለማገድ ወይም ለመሠረዝ ያቀደ እንደሆነ፣ ባለፈቃዱ ሊወሰድ የታቀደውን እርምጃ እንዲያውቀው ከ21 ቀናት በፊት የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት። ይህም ማስጠንቀቂያ እርምጃው እንዲወሰድ መንስኤ የሆኑትን ሁኔታዎች እና ፈቃድ የተሰጠው ሰው ማስተካከያ ሊያደርግባቸው የሚገባ ጉዳዮችን ጭምር የሚገልጽ መሆን አለበት። ፈቃድ የተሰጠው ሰው ማስጠንቀቂያው በደረሰው በ21 ቀናት ጊዜ ውስጥ በታክሱ ባለሥልጣን የተጠየቁ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት።

የታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የወሰዳቸውን የማስተካከያ እርምጃዎች የሚመለከት ሪፖርት በደረሰው በ14 ቀናት ውስጥ የተወሰዱት እርምጃዎች በቂ መሆናቸውን ወይም በማስጠንቀቂያው የተገለፁ እርምጃዎች የሚወሰዱ መሆኑን ለመግለጽ ይችላል። በማስጠንቀቂያው የተገለፁ እርምጃዎች የሚወሰዱ መሆኑን እንዲያውቀው የተደረገ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በታክስ ባለሥልጣኑ ውሣኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ፣ ውሣኔው ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በ10 ቀናት ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ለታክስ ባለሥልጣኑ የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ሊያቀርብ ይችላል። የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል አቤቱታው በደረሰው በ10 ቀናት ጊዜ ውስጥ በቀረበው ቅሬታ ላይ ውሣኔ መስጠት አለበት። ፈቃድ የተሰጠው ሰው በአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል በተሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ውሣኔው በተገለፀለት በ14 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለግብር ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችል ሲሆን፣ የይግባኙ ማመልከቻ በ7 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን እንዲደርስ ማድረግ አለበት።

## 3.15. ስለይግባኝ

የግብር ይግባኝ ኮሚሽን የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት። በግብር ይግባኝ ኮሚሽን የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ የሚያምን ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የታክስ ባለሥልጣን ውሳኔው በተሰጠ በ30 ቀናት ጊዜ ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

**መኪራ አራት**

1. የኤክሣይዝ ታክስ ምዝገባ እና ፈቃድ እንዲሁም እገዳን ግለጹ?

# ክፍል አራት የኤክሳይዝ

## ታክስ ቁጥጥር

### 4.1.የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

ፈቃድ በተሰጠው አምራች ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በታክስ ባለሥልጣኑ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር (ከዚህ በኋላ "የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር" በሚል የሚጠራ) ይደረግባቸዋል። የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር የሚደረገው ከሚከተሉት በቀደመው ጊዜ ይሆናል:-

- ፈቃድ በተሰጠው አምራች ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከፋብሪካው እስከሚወጡ፣
- ዕቃዎቹ ከኢትዮጵያ ውጪ እስከሚላኩ፣ ወይም
- ዕቃዎቹ ከአገልግሎት ውጪ እስከሚደረጉ ወይም እስከሚወገዱ ድረስ።

ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር እስካሉ ድረስ፣ በታክስ ባለሥልጣኑ ሥልጣን የተሰጠው የባለሥልጣኑ ሠራተኛ በማናቸውም ጊዜ ዕቃዎቹን መመርመር ይችላል። በታክሱ ባለሥልጣን ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማናቸውም ሰው ዕቃዎቹን ከፋብሪካ ማውጣት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ዕቃዎቹን የሚመለከት ማናቸውንም ተግባር መፈፀም አይችልም። ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር ባሉበት ጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን የዕቃው ባለቤት ዕቃዎቹን ለታክሱ ባለሥልጣን እንዲያስረክብ ሊጠይቅ ይችላል። የታክሱ ባለሥልጣን ዕቃዎቹን ከተረከበ በኋላ ዕቃዎቹ በታክሱ ባለሥልጣን በሚሰጥ መመሪያ መሠረት በባለቤቱ ወጪ ሊሸጡ ወይም ከአገልግሎት ውጪ እንዲሆኑ ሊደረግ ወይም ሊወገዱ ይችላል።

### 4.2. በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ሥር ያሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በሚመለከት ፈቃድ የተሰጠው አምራች ግዴታዎች

የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በተገቢው የሂሳብ አያያዝ የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የተፈቀደለት አምራች:-

- የታክሱ ባለሥልጣን በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም ጥሬ ዕቃዎችን ለመመዝገብ፣ ክብደታቸውን ለመለካት፣ ለመቆጣጠር፣ ለመቁጠር እንዲችል ወይም እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተመሳሳይ የቁጥጥር ሥራዎችን

እንዲያከናውን በፋብሪካው ውስጥ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያዎች እንዲኖሩ እና በሚገባ እንዲጠበቁ ማድረግ፤

- በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የተሟላ ቁጥጥር ለማድረግ በሚያስችል መንገድ ማስቀመጥ፤
- በፀደቀው ቅጽ መሠረት የጥሬ ዕቃዎችን ምዝገባ ማካሄድ፣ በተለይም በማምረት ሂደት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፋብሪካው የተረከባቸውን ጥሬ ዕቃዎች እና ግብአቶች በእነዚህ ቅፆች ላይ መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት ማረጋገጥ፤
- በፀደቀው ቅጽ መሠረት የመጨረሻ ምርቶችን ምዝገባ ማከናወን፣ እና በዚሁ ቅጽ ላይ በፋብሪካው የተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች እና ከፋብሪካው የወጡ ዕቃዎችን መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት ማረጋገጥ፤
- የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ በዋሉ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ መሆኑን ማረጋገጥ፤

የታክሱ ባለሥልጣን አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማናቸውም ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ናሙና ከአምራቹ በነፃ የመውሰድ መብት ያለው ሲሆን፣ እነዚህ ናሙናዎች የታክስ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ሊወገዱ ወይም ለአምራቹ ሊመለሱ ይችላሉ። በጽሑፍ በሚወሰነው አኳኋን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ባለቤት የኤክሳይዝ ታክሱን ሳይከፍል ለገበያ በማይውል መጠን ከፋብሪካው ናሙናዎችን እንዲወስድ ሊፈቅድ ይችላል።

### 4.3. ከአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጪ የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን መያዝ ወይም መጠቀም የተከለከለ ስለመሆኑ

ፈቃድ ከተሰጠው የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጪ ማናቸውም ሰው የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን መያዝ ወይም መጠቀም አይችልም። የታክሱ ባለሥልጣን የሚጥላቸው አስገዳጅ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጪ ሌላ ሰው የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ እንዲይዝ ወይም እንዲጠቀምበት ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል:-

- የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን ለሽያጭ የሚያመርት ወይም የሚይዝ ሲሆን፤

- መሣሪያው የተያዘው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው ለሙከራ፣ ለጥናት ወይም ለሳይንሳዊ ምርምር ዓላማ ሲሆን፤
- የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያው የተያዘው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው ከአልኮል መጠጦች ውጪ የሆነ ሌላ ምርት ለማምረት ሲሆን።

## 4.4. ከፋብሪካ ወጪ እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ዕቃዎች

የተፈቀደለት አምራች የታክሱን ባለሥልጣን በሚያረካ አኳኋን በፋብሪካው የተመረተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት በማስረጃ ማረጋገጥ ያልቻለ እንደሆነ፣ በአንድ ወር ውስጥ ተመርቷል በተባለው እና ሊመረት ይችላል ተብሎ በሚታመነው መካከል ያለውን ዕቃ ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጪ ከፋብሪካው ወጪ እንዳደረገ ይቆጠራል። የተፈቀደለት አምራች በትክክል ባመረተው እና የተመረተ ዕቃ በሚመዘገብበት ሰነድ ላይ በተመዘገበው መካከል ልዩነት መኖሩን ያወቀ እንደሆነ፣ ይህንኑ ወዲያውኑ ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።

## 4.5. በማምረቻ ቦታዎች ወይም በማስተላለፊያ መስመሮች ላይ ምልክት ስለማድረግ

- የተፈቀደለት አምራች:-

ሀ) የታክሱ ባለሥልጣን በሚጠይቀው መሠረት በማምረቻ ቦታው ዋና የመግቢያ በር እና በሌላም አስፈላጊ ቦታ ላይ በአማርኛና በአካባቢው የሥራ ቋንቋ:-

(i) “የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማምረቻ” እና

(ii) የተፈቀደለትን አምራች ስም እና የፈቃድ ቁጥር የያዘ ፅሑፍ መለጠፍ አለበት።

ለ) በምርቱ ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ የማስተላለፊያ መስመሮች በቋሚነት የተገጠሙ እና መላውን ርቀት በትክክል ለመመርመር የሚያስችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

ሐ) የማከማቻ እና የማስተላለፊያ መስመሮች ኢንዱስትሪው የሚጠየቀውን ደረጃ የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

መ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በሚመረቱባቸው፣ ለሽያጭ በሚዘጋጁባቸው ወይም በሚከማቹባቸው መሣሪያዎች ላይ በዘይት ቀለም ምልክት ማድረግ አለበት።

ሠ) የተፈቀደለት አምራች የታክሱን ባለሥልጣን በሚያረካ ሁኔታ እያንዳንዱን ማከማቻ ወይም መሣሪያ ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች አኳኋን ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ የተገጠመባቸው እንዲሆን ማድረግ አለበት።

ረ) ለኤክሳይዝ ታክስ አሰባሰብ ሲባል መቆለፍ ወይም ማሸግ እንዲቻል የታክሱ ባለሥልጣን በሚጠይቀው መሠረት መሣሪያዎችን ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ በሚያስችል መንገድ ማዘጋጀት አለበት፡፡

ሰ) የታክሱን ባለሥልጣን በሚያረካ ሁኔታ:-

(i) በእያንዳንዱ የማምረት ሂደት የምርት ርክክብ የሚፈፀምባቸው የማስተላለፊያ መስመሮች በተለያየ የዘይት ቀለም እንዲቀቡ እና ቀለሙ እንዳይጠፋ በየጊዜው እንዲታደስ ማድረግ አለበት፡፡

(ii) ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች ሁኔታ እያንዳንዱ ማከማቻ ወይም መሣሪያ ማስቀመጥ እና በውስጣቸው የያዙትን መጠን ማወቅ የሚያስችል የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያ መግጠም፣ አለበት፡፡

ሸ) ለ (ሰ) አፈፃፀም የማጣሪያ ፋብሪካ ባለቤት በተሟላ አኳኋን እና ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መንገድ የማስተላለፊያ መስመሮችን የሚከተለውን የዘይት ቀለም ዓይነት መቀባት አለበት:-

| | | |
|---|---|---|
| (i) | የአልኮል መጠጥ | - ቀይ |
| (ii) | ቢራ | - ሰማያዊ |
| (iii) | ሞላሰስ | - አረንጓዴ |
| (iv) | የሚጠራ ወይን | - ቡናማ |
| (v) | ውሃ | - ቢጫ |
| (vi) | ናፍጣ | - ጥቁር |

ቀ) ለታክሱ ባለሥልጣን አስቀድሞ በማስታወቅ ከታክሱ ባለሥልጣን ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር የአመራረቱን ሂደት ወይም አካሄዱን መለወጥ፣ ማከማቻ ወይም መሣሪያ መጨመር የለበትም፡፡

በተፈቀደለት የማምረቻ ቦታ የጽሕፈት ሥራ የሚከናወንበት ቢሮ፣ የማምረቻው ቦታ፣ የጥሬ ዕቃ መጋዘን፣ የምርት መጋዘን የተለያየ መሆን አለባቸው፡፡ ለዚህ አፈፃፀም ለእያንዳንዱ ተግባር የተመደበው ቦታ ጥበቃ የሚደረግለት እና አንዱ ከሌላው ጋር የማይገናኝ እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክስን በሚገባ መሰብሰብ እንዲቻል ለይቶ ለመቆለፍ ወይም ለማሸግ የሚያስችል አካል የተገጠመለት መሆን አለበት፡፡ ማናቸውም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት የተፈቀደለት አምራች እና የተመዘገበ አስመጪ ወደ ሀገር የሚያስገባቸውን ዕቃዎች የሚያከማችበት በታክሱ ባለሥልጣን የተፈቀደ የተለየ መጋዘን ሊኖረው ይገባል፡፡

### 4.6. ፋብሪካውን በሩቅ መቆጣጠር የሚያስችል መሣሪያ ስለመግጠም

የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ የሚከናወነውን እንቅስቃሴ በሩቅ ማየት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሥርዓት መግጠም አለበት፡፡ የታክሱ ባለሥልጣን ሊገጠም የሚገባውን የቴክኖሎጂ መሣሪያ ዝርዝር ባህሪያት ይወስናል፡፡ ለዚህ አፈፃፀም የታክሱ ባለሥልጣን ፋብሪካውን በሩቅ ማየት የሚያስችለውን የቴክኖሎጂ ሥርዓት የመጠቀም ያልተገደበ መብት ይኖረዋል፡፡ በዚህ የተመለከተው የቴክኖሎጂ ሥርዓት የታክስ ባለሥልጣኑ በሚጠይቀው መሠረት ደህንነቱ የተጠበቀ የምስል ማከማቻ እና ምስልን እና ሌላን መረጃ በዲጂታል ሥርዓት በቀጥታ ማስተላለፍ የሚችል መሆን አለበት፡፡

### 4.7. የአመራረት ሂደትን በቴክኖሎጂ ስለማስደገፍ

የታክሱ ባለሥልጣን የተወሰኑ የተፈቀደላቸው የማምረቻ ቦታዎች በእያንዳንዱ ደረጃ ያሏቸው የአመራረት ሂደት በአውቶማቲክ የአመራረት ሂደት የታገዘ እንዲሆን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የአልኮል መጠጥ ማምረቻ ፋብሪካዎችን በሚመለከት ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ግዴታ ሊጣልባቸው የሚችለው የፋብሪካው የማምረት አቅም በሰዓት ከ 6,000 ጠርሙስ በላይ ሲሆን ነው፡፡

### 4.8. የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች

የታክሱ ባለሥልጣን፤ በማምረቻ ቦታዎች ሊታከሉ የሚገባ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ እንዲሁም ሌሎች መሣሪያዎችን ተፈላጊ ባህሪያት በጋዜጣ እና በድረገፁ ላይ ማሠራጨት አለበት፡፡ በታክሱ ባለሥልጣን የሚፈቀዱት በማምረት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች የጥሬ ዕቃዎችን፣ የግብዓቶችን እና የአላቂ ዕቃዎችን መጠን በትክክል ማወቅ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡ የጥሬ ዕቃ እና የአላቂ ምርቶች ማከማቻ ጋኖች በጋኑ ውስጥ ያለውን መጠን በትክክል ማወቅ የሚያስችል የመቆጣጠሪያ ሥርዓት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡ ጥቅም ላይ የሚውሉ የመቁጠሪያ እና የመለኪያ መሣሪያዎች የታክሱ ባለሥልጣን በሚወስነው መሠረት በምርቱ ሂደት በእያንዳንዱ የምርት ሠንሰለት ላይ መገጠም አለባቸው፡፡

የተፈቀደለት አምራች፤ የታክሱ ባለሥልጣን ለሚያካሂደው ቁጥጥር እና ስሌት በሚያመች መንገድ መቁጠሪያ እና መለኪያ ያላቸውን ጋኖች ወይም ማከማቻዎች የማዘጋጀት፣ በትክክል የሚሠሩ መሆኑን በየጊዜው የማረጋገጥ፣ እና በመለኪያ እንዲሁም በመቁጠሪያ መሣሪያዎች ላይ ፈቃድ በተሰጠው ባለሙያ የተደረገውን ዕድሳት የሚያሳይ መዝገብ

የማዘጋጀት፣ መሣሪያዎቹ በትክክል የሚሠሩ መሆኑን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡

## 4.9.በምርቶች፣ በመያዣዎች እና በማሸጊያዎች ላይ ምልክት (ሌብል) ስለማድረግ

ከታክስ ነፃ የሆኑ፣ ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማሸጊያዎች ለመከታተል እና ለይቶ ለማወቅ በሚያስችል አኳኋን የተለየ ምልክት ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ ለጅምላ ሽያጭ የሚውሉ ዕቃዎችን የሚይዝ እያንዳንዱ ማሸጊያ ወይም መያዣ ወይም መጠቅለያ በሚከተለው አኳኋን ህትመት ሊደረግበት ይገባል:-

- ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ከሆነ፣ የመጨረሻ መድረሻውን ሀገር የሚያሳይ ጽሑፍ፣
- በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ፣ "ለሀገር ውስጥ ፍጆታ" የሚውል የሚል ጽሑፍ፣
- ከቀረጥ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች ለሚሸጡበት መደብር ወይም ለዲፕሎማቲክ ሱቆች የሚሸጥ ከሆነ "ከታክስ ነፃ" የሚል ጽሑፍ:: ለዚህ አፈፃፀም የታክሱ ባለሥልጣን ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ ዕቃዎችን ለመለየት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ሊደረግ የሚገባውን ምልክት ሊወሰን ይችላል፡፡

## 4.10. በጥሬ ዕቃ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት የሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች መጠናቸውን በትክክል ለማወቅ ለሚደረገው ቁጥጥር በሚያመች አኳኋን ደህንነቱ በተጠበቀ ክፍል ወይም መጋዘን መቀመጥ አለባቸው፡፡ በተፈቀደለት ማምረቻ ውስጥ ለምርት ተግባር እንዲውሉ ለማድረግ ወይም አደጋ በማጋጠሙ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ሳይፈቀድ ጥሬ ዕቃዎችን ማውጣት አይችልም፡፡ የአልኮል ማጣሪያ ባለቤት ከኤቲል አልኮል በስተቀር ማናቸውንም ሌላ አልኮል በታክሱ ባለሥልጣን በሚወሰነው መሠረት ለሰው ጥቅም እንዳይውል ከመደረጉ በፊት በመጋዘን ማስቀመጥ አይችልም፡፡

## 4.11. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከተመረቱ በኋላ በመጋዘን ስለማስቀመጥ ወይም ስለማስረከብ

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረት ተግባር ከተጠናቀቀ በኋላ "የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ" በመባል ወደሚታወቅ ክፍል መዘዋወር እና

ከተፈቀደለት ፋብሪካ ቅጥር ግቢ ውጪ እስከሚደረጉ ድረስ በዚሁ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለባቸው። ሆኖም የተጣራ አልኮል መቀበያ ጋኖች የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ እንደሆኑ ይቆጣራል። የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል በር ላይ "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል" የሚል ጽሑፍ መለጠፍ አለበት። የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን የተመረቱ ዕቃዎች ከማከማቻነት ውጪ ለሌላ ለማናቸውም ተግባር እንዲውል ማድረግ አይቻልም።

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ለቁጠራ በሚያመች አኳኋን በኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል ውስጥ መቀመጥ አለባቸው። ማናቸውም ሰው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልበት ዕቃ መያዣ ጠርሙስ ወይም ማሸጊያ አምራቹን ለይቶ ማወቅ የሚያስችለው ልዩ ምልክቱ (ሌብል)፣ የአምራቹ ስም፣ የተመረተበት ቦታ እና ቀን፣ አድራሻው፣ የተከታታይ ምርት ቁጥር፣ የባር ኮድ ወይም ሌላ ተጨማሪ ምልክት ሳይደረግበት በፊት ከኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎች ማከማቻ ክፍል ማውጣት ወይም እንዲወጣ ማድረግ ወይም መፍቀድ የለበትም። ለውጭ ገበያ ወይም ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው ሊሸጡ የተመረቱ ዕቃዎች ለቁጥጥር እና ለክትትል በሚያመች መንገድ ከሌሎች ዕቃዎች ተለይተው መቀመጥ አለባቸው። የተፈቀደለት አምራች ከተሸጡ በኋላ ወደተመረቱበት ፋብሪካ የተመለሱ ዕቃዎች የሚቀመጡበት የተለየ መጋዘን ሊኖረው ይገባል።

## 4.12. ለውጭ ገበያ እና ከታክስ ነፃ ሆነው የሚሸጡ ዕቃዎች

- የተፈቀደለት አምራች የሚከተሉትን ሁኔታዎች ካጋጠሙ በዕቃዎቹ ላይ ታክሱን እንዲከፍል ይገደዳል:-
  - ሀ) ለውጭ ገበያ የተመረቱ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ የተሸጡ እንደሆነ፣
  - ለ) ከታክስ ነፃ ሆነው ስለሚሸጡበት ወይም ታክሱ ተመላሽ ስለሚደረግበት ሁኔታ በአዋጁ የተመለከተው ያልተሟላ እንደሆነ።

የተፈቀደለት አምራች ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ እና የተከፈለባቸው ታክስ ተመላሽ የሚደረግ ዕቃዎችን የማስታወቅ እና የማጓጓዝ ኃላፊነት አለበት። ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ የአልኮል መጠጦችን የሚሸጥ የቀረጥ ነፃ መደብር እነዚህን ዕቃዎች ወደ ሀገር ለማስገባት የሚችለው "ከቀረጥ ነፃ" የሚል ምልክት የተደረገባቸው ሲሆን ብቻ ነው።

## 4.13. ልዩ ምልክትን (ሌብል) ስለማሳወቅ

ማናቸውም የተፈቀደለት ሰው በተፈቀደው ቅጽ መሠረት እና የታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው እና በሚያፀድቀው ዝርዝር መሠረት ልዩ ምልክቱን ሳያስታውቅ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ለሽያጭ በጠርሙስ ወይም በሌላ መያዣ ማሸግ አይችልም። ይህ ቢኖርም የታክሱ ባለሥልጣን ማመልከቻ ሲቀርብለት ሁኔታዎችን በመወሰን የተፈቀደለት አምራች ለሙከራ የሚውሉ ምርቶችን እንዲያመርት ሊፈቅድ ይችላል።

## 4.14. የምርት መከታተያ ሥርዓት

- የታክሱ ባለሥልጣን የተፈቀደለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች አምራች ወይም አስመጪ የምርት ሂደቱን መከታተል የሚያስችል የሂሳብ ሥርዓት እንዲዘረጋ ሊያዝ ይችላል። የምርት መከታተያው ሥርዓት:-

ሀ) የምርትን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ወይም ማሳየት የሚያስችል መሣሪያ፣

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን በተፈቀደለት አምራች የተመረቱ ወይም ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ ዕቃዎችን ብዛት ለመቆጣጠር፣ ለመመዝገብ እና መረጃውን ለማስተላለፍ የሚያስችል መሣሪያ መሆን አለበት።

- የምርት መከታተያው ሥርዓት:-

ሀ) በማምረቻው ቦታ በምርት ሠንሰለት ውስጥ በእያንዳንዱ የማሸጊያ ወይም የማተሚያ መሣሪያ ላይ ሊገጠም፣ እና

ለ) ወደ ሀገር የሚገቡ ዕቃዎችን ለመቆጣጠር በታክሱ ባለሥልጣን በሚወስነው አኳኋን ሊገጠም ይገባል።

- አዲስ ወይም የተሻሻለ የምርት መከታተያ ሥርዓት መግጠም አስፈላጊ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ የታክሱ ባለሥልጣን ለአምራቹ ወይም ለአስመጪው መሣሪያው ከሚገጥምበት ጊዜ በፊት የሚከተሉትን የያዘ ማስታወቂያ መስጠት አለበት:-

ሀ) አዲሱ መሣሪያ የምርት መከታተያውን ሥርዓት የተሻለ ለማድረግ አስፈላጊ መሆኑን፣ ለ) በእያንዳንዱ የምርት ሠንሰለት ውስጥ የሚደረገውን የማስተካከያ ሥራ ባህሪያት እና

ሐ) በኮምፒውተሮች እና በሌሎች መሣሪያዎች ላይ መሣሪያው የሚገጠምበትን እና የሚሠራበትን ሁኔታ፣

- የተፈቀደለት አምራች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ወይም የማይሠሩ የምርት መስመሮች በሚከተለው አኳኋን ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት:-

ሀ) የማይሠሩ መስመሮችን በ 24 ሰዓት ውስጥ፣ ወይም

ለ) አምራቹ ምርቱን ከ24 ሰዓት በላይ የሚያቋርጥ ከሆነ የምርት ሂደቱ በተቋረጠ በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ::

- የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የታክሱ ባለሥልጣን የምርት መስመሮችን መቆጣጠር አለበት:-

ሀ) የተፈቀደለት አምራች የምርት መስመሮች ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ወይም የማይሠሩ መሆኑን ካስታወቀ፣ ወይም

ለ) የምርት መስመሮች የማምረት አቅም ሙሉ በሙሉ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ::

- የታክሱ ባለሥልጣን፤ የምርት መስመሮችን የተቆጣጠረ በሚሆንበት ጊዜ የተፈቀደለት አምራች የታሸገው የምርት መስመር እንዲከፈትለት ለማድረግ አምራቹ ማምረት የሚጀምርበትን ቀንና ሰዓት ጭምር የያዘ የአመራረቱን የጊዜ ሠሌዳ የሚያሳይ ሪፖርት ለታክሱ ባለሥልጣን ማቅረብ አለበት።

**ሙከራ አምስት**

1. የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥርን ግለጻ አድርጉ?

## ክፍል አምስት

## ስለተመላሽ

### 5.1. ተመላሽ

በሀገር ውስጥ የተመረቱ ወይም ከውጭ ሀገር የመጡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ከተከፈለባቸው በኋላ ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ያጋጠመ መሆኑን የታክሱ ባለሥልጣን ያረጋገጠ እንደሆነ፣ በአምራቹ ወይም በአስመጪው በሚቀርብ የጽሑፍ ማመልከቻ መሠረት የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ሊደረግ ይችላል፤

- በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት:-
  - I. ወደ ኢትዮጵያ በመጓጓዝ ላይ እያሉ ዕቃዎቹ ከጥቅም ውጪ የሆኑ ወይም የተሠረቁ እንደሆነ፣
  - II. በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች ከጥቅም ውጪ የሆኑ ወይም የተሠረቁ እንደሆነ፣
  - III. በሽያጭ ውሉ መሠረት ገዢው ዕቃውን ለሻጩ የመለሰ እንደሆነ፣
- የኤክሳይዝ ታክስ ከተከፈለ በኋላ ፈቃድ በተሰጠው ወይም በተመዘገበ አምራች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን ለማምረት የዋሉ እንደሆነ፣

የተፈቀደለት ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከላይ የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክሱን የከፈለ እና ለእነዚህ ዕቃዎች ከገዢው ምንም ዓይነት ክፍያ ያልተቀበለ መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጥ የቻለ እንደሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክሱ ተመላሽ እንዲደረግለት ለባለሥልጣኑ በፅሑፍ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል። የታክሱ ባለሥልጣንም የተፈቀደለት ሰው በእነዚህ ዕቃዎች ላይ ምንም ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ ያልተቀበለ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል።

የሚቀርበው የተመላሽ ጥያቄ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በቀደመው ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት:-

ሀ) ዕቃዎቹ ከተሸጡበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፣ ወይም ለ) ገዢው በሕግ የከሠረ መሆኑ በተረጋገጠበት ጊዜ፣

በዚህ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርበው ማመልከቻ:-

- በፀደቀው ቅጽ መሠረት እና
- በታክሱ ባለሥልጣን በሚወሰነው አኳኋን ሆኖ፣ የሚቀርብ የተመላሽ ጥያቄን በሚመለከት የኤክሳይዝ ታክሱ በተከፈለ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት። በዚህ መሠረት ተመላሽ የሚደረገው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን የሚወሰነው በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሠረት ይሆናል። ወደ ሀገር ከገቡ በኋላ ተመልሰው ወደ ውጭ ሀገር በተላኩ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ ከሆነ ወደ ውጭ በተላኩት ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ታክስ በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ተመላሽ ይደረጋል። የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ከተደረገ በኋላ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከገዢው ላይ የኤክሳይዝ ታክሱን በሙሉ ወይም በከፊል የተቀበለ ከሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክሱን በተቀበለ በ30 ቀናት ውስጥ በተቀበለው መጠን ተመላሽ የተደረገለትን የኤክሳይዝ ታክስ ለታክሱ ባለሥልጣን መመለስ አለበት።

## 5.2. ተመላሽ የተከፈለባቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የተሸጡ ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጪ ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ስለመሆኑ

የተመላሽ ክፍያ የተፈፀመባቸው ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ተመላሹ ከተከፈለ በኋላ የተሸጡ ወይም ተመላሹ ከተፈቀደበት ዓላማ ውጪ ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ፣ ተመላሹ ባይፈቀድ ኖሮ ዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል ይገባ በነበረው ልክ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል። ለማናቸውም ዓላማ የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ክፍያ የተፈፀመበት ዕቃ በእጁ የገባ ሰው፣ ዕቃውን ተመላሹ ከተፈቀደበት ዓላማ ውጪ ለመጠቀም ወይም ለመሸጥ፣ የፈለገ እንደሆነ፣ ዕቃው የሚሸጥበትን ወይም ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዝርዝር ሁኔታ በሚመለከት ለታክሱ ባለሥልጣን ሪፖርት ማቅረብ እና በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል አለበት።

## 5.3. ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች ተመልሰው ወደ ሀገር የገቡ ወይም ለሽያጭ የዋሉ እንደሆነ ታክሱ የሚከፈል ስለመሆኑ

የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደ ውጭ ሀገር ከተላኩ ወይም በዓለም ዐቀፍ ትራፊክ ለመንገደኞች አገልግሎት እንዲውሉ በአውሮፕላን ላይ ከተጫኑ በኋላ፣ ለሀገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ከጭነት የተራገፉ እንደሆነ፣ አስመጪው ዕቃዎቹ በተራገፉበት ጊዜ ፀንቶ ባለው የማስከፈያ መጣኔ መሠረት በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል አለበት። የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከታክሱ ነፃ

ተደርገው ወደሀገር ከገቡ ወይም ከተሸጡ በኋላ ተመልሰው ለሽያጭ ከዋሉ ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጪ ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል።

## 5.4. ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች ተመልሰው የተሸጡ ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጪ የዋሉ እንደሆነ ታክሱ የሚከፈል ስለመሆኑ

ማናቸውም ሰው ከዚህ ሞጁል ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ 2 ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎችን ወደ ሀገር ካስገባ ወይም ከገዛ በኋላ ዕቃዎቹን መልሶ የሸጠ ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጪ ጥቅም ላይ ያዋለ እንደሆነ ዕቃዎቹ በተሸጡበት ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጪ ጥቅም ላይ በዋሉበት ቀን ፀንቶ በሚሠራበት የማስከፈያ ልክ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል አለበት። ይህ ቢኖርም ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው ወደ ሀገር የገቡ ተሽከርካሪዎችን በሚመለከት ከታክስ ነፃ መብት የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው የሞተ እና ተሽከርካሪው በውርስ ለወራሾች የተላለፈ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክሱ አይከፈልም።

**ሙከራ ስድስት**

1. የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ስለማድረግ የሕግ አግባቡን በማስረዳት ተመላሽ የሚፈቀድባቸውን ግብዩቶች ለዩ?

## ክፍል ስድስት የኤክሳይዝ

## ታክስ አስተዳደር

### 6.1. መዝገብ ስለመያዝ

የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ማናቸውም ሰው የሂሳብ መዝገብ የመያዝ እና ጠብቆ ማቆየት ግዴታ አለበት። በዚህ መሠረት መያዝ ያለበት የሂሳብ መዝገብ፣

- በሚነበብ እና ሊጠፋ በማይችል አኳኋን በጽሕፈት መሣሪያ የተዘጋጀ፣ የታተመ ወይም የተፃፈ ሊሆን የሚገባው ሲሆን፣ ከመፅደቁ በፊት የተደረገ እርማት ወይም ለውጥ ሲኖር የተደረገውን ለውጥ ወይም እርማት በትክክል ለማወቅ የሚያስችል፣ እርማቱን ያከናወነው ሰው ፊርማ እና የታረመበት ቀን የተፃፈበት፣
- በተፈቀደ አኳኋን በኤሌክትሮኒክ ወይም በሌላ መንገድ የተዘጋጀ እና በተፈቀደው አኳኋን ካልሆነ በስተቀር ለውጥ ያልተደረገበት መሆን አለበት።

የታክሱ ባለሥልጣን በአዋጁ ወይም በመመሪያ ከተመለከተው ውጪ የተዘጋጀን የሂሳብ ሰነድ ወይም ማስረጃ ላለመቀበል ወይም በዚህ ሰነድ መሠረት ሥራዎችን ላለማከናወን ይችላል። የታክሱ ባለሥልጣን ማናቸውም የሂሳብ ሪፖርት ሊቀርብ የሚገባበትን ቅጽ ወይም ለአፈፃፀም ተቀባይነት የሚኖራቸውን ሰነዶች ዓይነት ሊወስን ይችላል።

### 6.2. የኤክሳይዝ ታክስን ስለማስታወቅ

በማናቸውም አንድ ወር የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈል ቢሆንም ባይሆንም የተፈቀደለት አምራች የእያንዳንዱን ወር ሂሳብ የሚቀጥለው ወር 30 ኛው ቀን ከማለፉ በፊት በፀደቀው ቅጽ እና በታዘዘው አኳኋን ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።

### 6.3. የኤክሳይዝ ታክስን የመክፈል ግዴታን ስለመወጣት

የተፈቀደለት አምራች በአንድ ወር ውስጥ ከማምረቻው ፋብሪካ ወጪ ባደረጋቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚቀጥለው ወር 30 ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት። አስመጪ ወደ ሀገር ውስጥ ባስገባቸው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎቹ ወደ ሀገር በገቡበት ጊዜ ለታክሱ ባለሥልጣን መክፈል አለበት። ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ታክሱ የሚሠላው፣ የሚከፈለው፣ ሂሳቡ የሚያዘው እና የታክሱ ዕዳ በአስገዳጅነት የሚሰበሰበው በጉምሩክ ሕግ መሠረት ይሆናል።

## ሙከራ ሰባት

1. የኤክሳይዝ ታክስ እንዴት እና መቼ ይከፈላል?

## ክፍል ሰባት

## የወንጀል ጥፋቶች እና አስተዳደራዊ ቅጣቶች

### 7.1. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

- ፈቃድ ሳይኖረው የኤክሣይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት ሊከፍል የሚገባውን የኤክሣይዝ ታክስ እጥፍ፣
- የኤክሣይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገባ ዕቃዎችን ቴምብር ሳይለጠፍባቸው የተገበያየ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ እጥፍ፣
- በፈቃዱ ከተመለከተው ቦታ ውጪ ሲያመርት የተገኘ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ እጥፍ፣
- ከኤክሣይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጪ ዕቃ ወጪ አድርጎ የተገኘ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ እጥፍ።

### 7.2. የወንጀል ቅጣቶች

- ፈቃድ ሳይኖረው የሚያመርት፣ የኤክሣይዝ ቴምብር ሳይለጥፍ የተገኘ፣ ከተፈቀደለት ቦታ ውጪ የሚያመርት ተላልፎ መገኘቱ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ከ 3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 50,000 እስከ ብር 100,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።
- የተፈቀደለት አምራች በፈቃዱ ከተመለከተው ሥፍራ ውጪ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ተግባር ላይ መሰማራቱ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ከ 5-7 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር 100,000-200,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።
- ፈቃድን እስከመታገድ የሚያደርስ ሁኔታ የተገኘ መሆኑ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ከ 1-3 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 100,000 ባልበለጠ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል።
- ማንኛውም ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጪ ከማምረቻው ፋብሪካ ወጪ ያደረገ እንደሆነ፣ ፈቃድ ሳይኖረው በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች ተከማችተው በሚገኙበት ቦታ የገባ እንደሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክሱ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጪ ባልተፈቀደ መንገድ ከተከማቹበት ቦታ ወጪ በማድረግ፣ ባህሪያቸውን በመለወጥ ወይም የቁጥጥሩን ሥራ በማወክ ረገድ የተባበረ፣ እንደሆነ፣ ጥፋተኛ

መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋጋጥ ከ5 - 7 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራትና ከብር 100,000 - 200,000 የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

- በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ከተደነገገው ውጪ የተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከተመረቱበት ፋብሪካ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎችን የገዛ ወይም ሳይፈቀድለት እነዚህን ዕቃዎች የተቀበለ ወይም በይዞታው ሥር ያደረገ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለባቸውን ዕቃዎች ለሽያጭ በማዋል ተግባር የተሠማራ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረገገጥ ከ3-5 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር 100,000-200,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡
- ስለኤክሳይዝ ቴምብር የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ2-3 ዓመት በሚደርስ እስራት እና ከብር 50,000-100,000 በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

**ሙከራ ስምንት**

1. የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተጠቀሱትን አስተዳደራዊ እና ወንጀል ቅጣቶች ለዩ?

# ክፍል ስምንት

## ታክስ ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት

የታክሱ ባለሥልጣን:-

- የኤክሳይዝ ታክስ ላለመክፈል የሚያስችል ስምምነት የተደረገ መሆኑን፣
- ማናቸውም ሰው ይህንን ስምምነት በመጠቀም የታክስ ጥቅም ያገኘ መሆኑን፣
- የስምምነቱ ይዘት ሲመረመር፣ የስምምነቱ ዋንኛ ዓላማ ተዋዋይ ወይም ሌላ ማናቸውም ሰው የኤክሳይዝ ታክስ ጥቅም እንዲያገኝ መሆኑን መረዳት የሚቻል ከሆነ፣ የታክሱ ባለሥልጣን ስምምነቱ እንዳልተደረገ በመቁጠር የኤክሳይዝ ታክስ ጥቅም ያገኘው ሰው የኤክሳይዝ ታክሱን እንዲከፍል ሊወስን ይችላል። የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ ከተገለፀው ውሳኔ ላይ የደረሰ እንደሆነ ይህንኑ የሚገልጽ የውሳኔ ማስታወቂያ ታክሱን መክፈል ላለበት ሰው መላክ አለበት። በዚህ መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታው ከተቋቋመበት ወር የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው። ለዚህ አፈጻጸም፡-

    ሀ) “ስምምነት” በመግባባት የተፈፀመ፣ በግልጽ የተፈፀመ ወይም በትርጉም የሚደረስበት ወይም በሕግ ፊት ተፈፃሚነት ያለው ቢሆንም ባይሆንም ድርጊት፣ ውልን፣ ማመቻቸትን፣ ቃል ኪዳንን፣ ዕቅድን፣ የውሳኔ ሀሳብን ወይም ግዴታ መግባትን ይጨምራል።

    ለ) “የታክስ ጥቅም” ማለት:-

    I. የኤክሳይዝ ታክስ ከመክፈል ግዴታ ነፃ መሆንን ጨምሮ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን መቀነስ፣
    II. የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ የማግኘት መብትን ማቋቋም፣
    III. የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚፀናበትን ቀን ማዘግየት፣
    IV. የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ቀን በማዘግየት ሌላ ማናቸውንም ጥቅም ማስገኘት፣
    V. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያስገኝ ጥቅም፣

        ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ታክሱ የማይከፈልባቸው እንዲሆኑ ማድረግ፣
        ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች አነስተኛ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልባቸው ማድረግ።

**ሙከራ ዘጠኝ**

1. ታክሱን ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት ምን ማለት እንደሆነ አስረዱ?

# ማጠቃለያ

ታክሱ የሚጣለው በተወሰኑ የቅንጦት ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር በሚያስከትሉ እና በዋጋቸው መጨመር ምክንያት ፍጆታቸው በማይቀንስ ዕቃዎች ላይ ነው። የኤክሳይዝ ታክስ መጣል አስፈላጊነት የኅብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ፣ በአካባቢ ደህንነት ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ዕቃዎችን አጠቃቀም መቀነስ፣ ገቢ ለመሰብሰብ እና ሀብትን ለማደላደል ያገለግላል። በዚህ ሞጁል፤ የኤክሳይዝ ታክስ አከፋፈል፣ ስለፈቃድ፣ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር፣ ስለተመላሽ፣ የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር፣ የወንጀል ጥፋቶች እና አስተዳደራዊ ቅጣቶች እንዲሁም ታክስ ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት እና ሌሎች የኤክሳይዝ ታክስ ጠቃሚ ጉዳዮች ተዳሰዋል።

**ማጣቀሻ**

- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 67/2013
- የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012
- በደብዳቤ ቁጥር በቀን ከኦፕሬሽን ዘርፍ የተላከ የእክሳይዝ ታክስ ቅጻ ቅጾች
- በደብዳቤ ቁጥር በቀን ከገንዘብ እና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የተላከ መግለጫ

## አባሪ 1:-ኤክሳይዝ ታክስ አፈፃፀም የሚያገለግሉ ቅፆች

ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ
ገቢዎች ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Revenue
የሰነድ ቁጥር / Document Number

**ኤክሳይዝ ታክስ ማሳወቂያ/ EXCISE TAX DECLARATION**

**የግብር ጊዜን የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች/ DETAILS OF TAX PERIOD**

ያሳወቁበት ቀን / Date of filing

የማስወቂያ አይነት/ Return type ዋና/ Original የተከለሰ/ Revised

የታክስ ጊዜTAX PERIOD/ ወር MONTH/ ዓ.ም YEAR/

**የ ግብር ከፋይ ዝርዝር መግለጫTAX-PAYER DETAILS/**

የግብር ከፋዩ ስም
Name of organization or tax payer

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርTax-payer identification number (TIN)
ንዑስ መለያ ቁጥር ( ካለ)Sub-TIN, if any/
የኤክሳይዝ ታክስ ምዝገባ ቁጥር/ Excise tax registration number
የታክስ ወኪሉ ዝርዝር መረጃ DETAILS OF TAX AGENT/
የግብር ማስታወቂያው በሌሎች አካላት (የታክስ ወኪል) የተዘጋጀ ከሆነ ቀጥሎ ያሉትን ዝርዝር መረጃዎች ይሙሉ/
If the return has been prepared by tax intermediary (tax agent), then please provide the following details .
የግብር ከፋይ ወኪል የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/ Agent TIN
የታክስ ወኪል ማህበራት/ድርጅቶች አባል ከሆኑ/ If you are a part of any tax agent association/ organization/
የታክስ ወኪል ተቋም የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/ Organization TIN

የግብር ከፋይ ወኪል የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር/ Agent TIN

**ማረጋገጫ CERTIFICATION**

በዚህ ቅጽ ላይ የሰፈሩት ሁሉም መረጃዎች ትክክልና የተሟላ መሆኑን አረጋግጣለሁ/ I hereby certify that the information given in this form is true and complete. I understand that any miss-presentation is punishable by law.
ፊርማ/ **Signature**

**ቀን/ Date**

**ኤክሳይዝ ታክስ ማሳወቂ/EXCISE TAX DECLARATION**

10. የተሸጡ ምርቶች የኤክሳይዝ ታክስ መጠን (አባሪ 1)
    Excise tax on taxable goods (annex 1 e)
20. በወሩ የሚቀናነስ ኤክሳይዝ ታክስ(አባሪ 3)
    Excise tax credit for the month (annex 3g)
30. የወሩ የተጣራ ኤክሳይዝ ታክስ ተከፋይ
    Net amount to be paid (Line 10 – 20)

**በሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሙያ ብቻ የሚሞላ/ TO BE USED BY MINISTRY OF REVENUE ONLY**

የባለሙያው ሥም/ OFFICER'S NAME ______________________ SIGNATURE/ ፊርማ
የሥራተኛ መታወቂያ ቁጥር/ Employee ID DATE/ ቀን
የታክስ ማዕከል/ TAX CENTRE

## 3) ሰንጠረዥ ሐ፡ በወሩ የተቀናነሰ ኤክሳይዝ ታክስ ዝርዝር ሚዛን
## Schedule c: monthly off-set for excise tax

| ወር ፤ ዓ.ም<br>Month ,year (a) | በወሩ የተሸጡ ምርቶች የኤክሳይዝ ታክስ<br>Amount of sales for the month (b) | Excise tax paid on inputs of sold items<br>ለሽያጭ በቀረቡ ምርቶች ላይ የተከፈለ የኢ.ክሳይዝ ታክስ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የእቃው አይነት<br>Type of product (c) | ብዛት<br>Quantity (d) | የደረሰኝ/ ዲክላራሲዎን ቁጥር<br>Invoice/declaration Number (e) | ከባለፈው ወር የዞረ ክሬዲት<br>Excise tax credits forward from previous month (f) | በግብዓት ላይ የተከፈለ በወሩ የሚቀነስ የኤክሳይዝ ታክስ መጠን /Excise tax amount paid on input deducted for the month (g) | ለሚቀጥለው ምርት የሚቀነስ ኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ<br>Excise tax credits available for next production (h) |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |

ማሳሰቢያ

- የተፈጸመ የጥሬ እቃ ግዥ ላይ የተከፈለ ኤክሳይስ ታክስ የሚቀናነሰው በምርት ሂደት በግብዓትነት የተጠቀሙበት መጠን እና ሽያጭ የተከናወነበት ብቻ ሲሆን አልኮል፣ ሲጋራ እና ስኳር ላይ የተከፈለ ታክስ አይቀናነስም፡፡

መረጃውን ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ

ስም-----------------------

ፊርማ-----------

ቀን---------------------

ሀላፊነት------------------------

መረጃውን ትክክለኛ መሆኑን ያረጋገጠው ባለሙያ

ስም-----------------------

ፊርማ-----------------------

ቀን---------------------

ሰንጠረዥ ለ፡ በወሩ በግብዓት ላይ የተከፈለ ኤክሳይዝ ታክስ ዝርዝር መረጃ

**Schedule B: Excise tax paid on raw materials**

| ተ.ቁ No. | የግዥደረሰኝ/ዲክላራሲዎን ቁጥር/ Purchase invoice/declaration Number | የሻጭ ታ/መ/ቁ/ Seller TIN | ቀን/ Date | የእቃውአይነት/ Description | ብዛት/ Quantity | የገንዘብ መጠን/ Value | ኤክሳይዝ ታክስ / Excise tax (a) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | |

## አባሪ/ ATTACHMENTS/ ANNEX-1

ሰንጠረዥ ሀ: ዝርዝር የኤክሳይዝ ታክስ የሽያጭ መግለጫ ከታች በቀረበው ሰንጠረዥ ያስቀምጡ

**Schedule A: Please attach the detailed excise declarations in the format below**

| ተ.ቁ No. | የእቃው አይነት Type of Product | ሽያጭ/አቅርቦት : Sales/Delivery | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | መለኪያ Measure ment | ብዛት Quantity (a) | የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ Ex-factory price (b) | አጠቃላይ ታክስ የሚከፈልበት ዋጋ Total excisable value C=(a*b) | የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ Rate of Excise tax (d) | ኤክሳይዝ ታክስ Excise tax E=(c*d) |
| 1 | | | | | | | |
| 2 | | | | | | | |
| 3 | | | | | | | |
| 4 | | | | | | | |
| 5 | | | | | | | |
| 6 | | | | | | | |
| 7 | | | | | | | |
| 8 | | | | | | | |
| 9 | | | | | | | |
| 10 | | | | | | | |
| | ድምር / Total | | | | | | |

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገቢዎች ሚኒስቴር

# ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው በእጅ የሚገኙ ምርቶች (inventory) ማሳወቂያ ቅጽ

*(ለአንድጊዜብቻየሚሞላ)*
*(ለሀገርውስጥአምራቾችብቻ)*

ቀን ------------------------------

የግብር ከፋይ ስም-------------------------------

የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር-----------------------

አድራሻ ክልል------------ዞን/ክፍለከተማ----------------ወረዳ----------- የቤት ቁጥር---------- ስልክ ቁጥር-------------------------

| ተ.ቁ | በመጋዝን የሚገኝ የምርት አይነት | (ለ) መለኪያ | እስከ የካቲት 05 ቀን 2012 ድረስ ተመርቶ በመጋዝን የሚገኝ የምርት ብዛት (ሐ) ከጥር ወር የዞረ ተመርቶ በመጋዝን የሚገኝ የምርት ብዛት | | | እስከ የካቲት 05 ቀን 2012 ድረስ ተመርቶ በመጋዝን የሚገኝ የምርት ብዛት (ሐ) ከየካቲት 01 እስከ የካቲት 05 ቀን 2012 ድረስ ተመርቶ በመጋዝን የሚገኝ የምርት ብዛት | | | (መ) እስከ የካቲት 05 ቀን 2012 ተመርተዉ በማምረቻ ዋጋ መሰረት ታክስ የተከፈለባቸዉ የምርት ብዛት | | | ታክስ የተከፈለበት ደረሰኝ ቁጥር | እስከ የካቲት 05 ቀን 2012 ተመርተዉ በማምረቻ ዋጋ መሰ ታክስ ያልተከፈለበት የምርት ብ ሠ=(ሐ)-(መ ) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠ/ዋጋ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ | | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋ |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | | | | |
| ድምር | | | | | | | | | | | | | | | |

## የኤክሳይዝ ታክስ ዝርዝር መረጃ የትክክለኛነት ማረጋገጫ

ከላይ የተገለፀው ማስታወቂያና የተሰጠው መረጃ በሙሉ የተሟላና ትክክለኛ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ማቅረብ በግብር ሕጉችም ሆነ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የሚያስቀጣ መሆኑን እገነዘባለሁ፡፡

የግብር ከፋይ/ሕጋዊ ወኪሉ ስም______________________________
ፊርማ____________________________ቀን_______________

የግብር ከፋዩ ማህተም

**ለቢሮ አገልግሎት ብቻ**

ትክክለኛነቱን ያረጋገጠው ኦፊሰር

ስም --------------------
ፊርማ-----------------------------------ቀን------------------------

Ministry of Revenue

| ተ.ቁ | (ሀ) እስከጥር 30 ቀን 2012 ድረስ ተመረቶ በመጋዝን የሚገኝ የምርት አይነት | (ለ) መለኪያ | (ሐ) እስከ የካቲት 05 ቀን 2012 ድረስ ተመርቶ በመጋዝን የሚገኝ ምርት | | | (መ) በማምረቻ ዋጋ መሰረት ታክስ የተከፈለባቸዉ ምርት | | | ታክስ የተከፈለበት ደረሰኝ ቁጥር | ( ሠ ) ተመርተዉ በማምረቻ ዋጋ መሰረት ታክስ ያልተከፈለበት ምርት ( ሐ ) - ( መ ) | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ | | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | ጠቅላላ ዋጋ |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| ድምር | | | | | | | | | | | | |

አባሪ 2:- የኤክሳይዝ ታክስ መጣኔ ሠንጠረዥ

| አንቀጽ | የታሪፍ ቁጥር | የዕቃው ዓይነት | ታክስ መጣኔ |
|---|---|---|---|
| **1. ስብና ዘይት** | | | |
